ሰኔ11 2016 ዓ.ም

ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች

የ2015 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት

የተከበሩ አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ የመንግስት ወጪ አስተዳደር ቁ/ጉ/ቋ/ኮ/ሰብሳቢ!

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀፅ 2 እና መሥሪያ ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 አንቀጽ 5 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 15፤ እንዲሁም በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1146/2011 አንቀጽ 2 ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተሰጠው ስልጣን መሰረት መ/ቤቱ ኦዲት ያደረገውንና ያስደረጋቸውን የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርት፣ የፌዴራሉ መንግሥት ለክልሎች ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ፣ ለመልሶ ማቋቋምና ለልማት ማስፋፊያ ለሚያስፈልጋቸው ወጪ የሚያደርገውን ድጎማ፣ በኢንቨስትመንት ፋይናንሲንግ የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች፣ የመንግሥት መ/ቤቶች አሠራር ህጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ፣ ተፈላጊውን ግብ የመታና ውጤት ያስገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ የተደረገውን የክዋኔና አካባቢ ኦዲት፣ እንዲሁም ስለመ/ቤቱ አጠቃላይ ሥራዎች ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ዓመታዊ ሪፖርት እንደሚያቀርብ በተደነገገው መሠረት የተከናወነ ነው።

በዚህ የ 2015 በጀት አመት ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት፤

1. በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ ላይ የተከናወኑ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት ፣ የፌዴራሉ መንግሥት ለክልሎች ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ፣ ለመልሶ ማቋቋምና ለልማት ማስፋፊያ ለሚያስፈልጋቸው ወጪ የሚያደርገውን ድጎማ ኦዲት ፣ የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲት፣ የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ የገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት እና ከተለያዩ አካላት የተጠየቁ የልዩ ኦዲቶች ፣ ሪፖርቶች ናቸው፡፡

2. ሪፖርቱ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ፈቃድ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት የተደረጉትን የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ሂሳብና በመንግስትና የልማት አጋር ድርጅቶች እርዳታና ብድር የሚካሄዱ ፕሮጄክቶች/ፕሮግራሞችን ኦዲት ያካትታል፡፡

3. የ2015/16 ኦዲት ዓመት የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ሂሣብ የኦዲት ዕቅድ ክንውን እና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣ የመሥሪያ ቤቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ፣ በኦዲት ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን አጭር የሥራ እንቅስቃሴን ያጠቃለለ ነው፡፡

4. የ2015 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ በመ/ቤታችን የተከናወኑ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርቶች ራሳቸውን ችለው በተጠናቀሩ 2 ጥራዞች የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው 7 መ/ቤቶችና የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው 15 መ/ቤቶች፣ እንዲሁም 32 አዳዲስ እና 11 ክትትልና በድምሩ 43 የክዋኔ ኦዲቶችን ለም/ቤቱ የቀረቡ ስለሆነ እነዚህን ሪፖርቶች የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች በሚገባ በመመርመር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል በጥልቀት ተዘጋጅቷል፡፡ በተጨማሪም የእነዚህ ሪፖርቶች ቅጅ 2 ጥራዞች /የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርት እና አጠቃላይ ዘገባ/ እና ሌሎች የተጠቀሱት ሪፖርቶች በሶፍት ኮፒ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤትም እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

5. እያንዳንዱ የኦዲት ሥራ እንደተጠናቀቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በኦዲቱ ግኝቶች ላይ የመውጫ ስብሰባ (Exit Conference) ከመደረጉም በተጨማሪ ረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት ተልኮላቸው መ/ቤቶቹ ለሥራ አመራር

ሪፖርቱ የሰጡትን ምላሽ ያገናዘበ በመሆኑ የመረጃዎቹ ተአማኒነትና አግባብነት በሁሉም ወገን ተቀባይነት እንዳለው ይታመናል፡፡

6. ኦዲቱ የተከናወነው በዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች ሲሆን፤ ለኦዲቱ መሰረት የሆኑት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት፣ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት፣ ሰነዶች፣ የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ሲሆኑ ኦዲቱም የተከናወነው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነትና አግባብነት ሙሉ በሙሉ ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

<u>ባለፈው አመት ኦዲት በተሰጠው አስተያየት መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች</u>

7. በ2014 በጀት ዓመት እና ከዚያ በፊት በተከናወኑ የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ92 መ/ቤቶች ተመላሽ እንዲደረግ ተብሎ አስተያየት ከተሰጠበት **ብር** 443,023,846.91 እና **በዶላር** 23,230.43 ውስጥ ተመላሽ የተደረገው **ብር** 48,217,965.67 መሆኑ ታውቋል፡፡

   ይህ አፈጻጸም ተመላሽ ሊደረግ ከሚገባው ሂሳብ ጋር ሲነፃፀር በመቶኛ 11 % ብቻ ሲሆን፤ ቀሪው **ብር** 394,805,881.56 እና **በዶላር** 23,230.43 ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደበትና ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ እንዲሁም በ2014 በጀት አመት የተሟላ ማስረጃ ሰነድ ካልቀረበበት **ብር** 5,061,185,100.80 ማስረጃ የቀረበበት **ብር** 508,157,756.13 ሲሆን በመቶኛ 10% ማስረጃው ቀርቦ ትክክለኛነቱ ተረጋግጧል፡፡ ምንም እንኳ የተመለሰው ገንዘብ አጥጋቢ ባይሆንም በተሰጠው አስተያየት መሰረት ጥረት በማድረግ አብዛኛውን ተመላሽ ያደረጉ ተቋማት፤ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ከተሰጠበት **ብር** 5,916,136.41 ውስጥ **ብር** 5, 862,031.32 (99.1 %)፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ከተሰጠበት **ብር** 4,157,768.79 ብር 3,503,190.47 (84.2%) እና የእስፔስ ሳይንስ ጂኦእሰፓሻል ሥልጠና ኢንስቲትዩት ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ከተሰጠበት **ብር** 5,603,804.28 ውስጥ **ብር** 4,463,361.87 (80%) ተመላሽ አድርጓል፡፡

8. የሰነድ ማስረጃ እንዲቀርብበት አስተያየት ከተሰጠባቸው አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ **ብር** 124,575,175.44 ሰነድ እንዲቀርብ ከተጠየቀበት ለብር 124,575,175.44 (100%)፣ የአደጋ ሥራአመራር ኮሚሽን ብር 150,257,928.96

(100%) እና አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ሰነድ እንዲቀርብበት ከተጠየቀ ብር 3,961,048.06 ውስጥ ብር 2,293,250.60 (58%) የተሟላ ሰነድ ቀርቦ ትክክለኛነቱ ተረጋግጧል።

9. የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ በ 2014/2015 በጀት አመት የተሰሩትን የፋይናንሻልና ህጋዊነት ኦዲትን እና የክዋኔ ኦዲትን ተለይቶ በቀረበለት ዉስጥ 21 ይፋዊ የህዝብ ስብሰባዎች እና 9 መስክ ምልከታዎች አካሂዷል፡፡ በዚሁ መሰረትም ይፋዊ ዉይይቱ በሚደረግበት ወቅትም የኦዲት ግኝቱን ባህሪ መነሻ በማድረግ አቅጣጫዎች የተቀመጡ ሲሆን የባለድርሻ አካላትም የተቋማቸዉን ተግባር እና ሃላፊነታቸውን መነሻ በማድረግ የሚከተሉትን እርምጃዎች ተወስዷል፡፡

ገንዘብ ሚኒስቴር በ2014 በጀት አመት ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት ከተሰጣቸው 19 መ/ቤቶች እና የኦዲት አስተያየት መስጠት ካልተቻለባቸዉ 6 መ/ቤቶች ዉስጥ በ6 ዩኒቨርሲቲዎች እና በ7 መ/ቤቶች ላይ የገንዘብ ቅጣት እና ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የሰጠ ሲሆን የ3 ዩኒቨርሲቲ ሃላፊዎች ከሃላፊነታቸው እንዲነሱ ተደርጓል። በተጨማሪም ትምርት ሚ/ር ከዋና ኦዲተር መ/ቤት በቀረበለት ጥያቄ መሰረት በኦዲት ወቅት ኦዲተሮችን በጥቅም ለመደለል የሞከሩትን የአንድ ዩንቨርስቲ የማኔጅመንት አባላት በሙሉ ከሃላፊነታቸው እንዲነሱ ተደርጓል፡፡

10. ምንም እንኳን ኦዲቱ በናሙና በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ማረጋገጫ መስጠት ባይቻልም በዚሁ አግባብ በተሰራዉ ኦዲት ለሶስት ተከታታይ አመት ከ2012 እስከ 2014 በጀት አመት አጥጋቢ ውጤት ላገኙ ለአራት ተቋማት፡ በገንዘብ ሚ/ር እውቅና ሰጥቷል፡፡

11. በ2014 በጀት አመት ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት አግኝተዉ የነበሩ በ2015 በጀት ዓመት አፈጻጸማቸውን በማስተካከል ነቀፌታ የሌለበት ኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው ተቋማት የፌዴራል ፀረ ሙስና ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ እስታትስቲክስ አገልግሎት፣ ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣ የግብርና ሚ/ር እና የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ሲሆኑ ለማመስገን እና በዚሁ አግባብ እንዲቀጥሉ ለማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

የ2015 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ኦዲት ዕቅድና ክንውን

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲትን በተመለከተ፣

12. በ2015 በጀት አመት በመ/ቤቱ አደረጃጀት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት የሚያደርጉ ስድስት ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች፣ የክልሎች ድጋፍና ድጎማ ሂሳብ ኦዲት የሚያደርግ አንድ ዳይሬክቶሬት እና በ1 የልዩ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በአጠቃላይ በ8 ዳይሬክቶሬት የተዋቀረ ሲሆን፤ ከየካቲት /2015 እስከ ጥር 30/2016 ድረስ በ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ አቅራቢ ከነበሩት 173 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች መካከል 162 መ/ቤቶችን እና 58 ቅርንጫፎች በመስሪያቤታችን የተቀሩትን 11ቹን ደግሞ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት በማስደረግ የኦዲት ሽፋኑን 100% ለማስቀጠል ታቅዶ የነበረ ቢሆንም 10 መ/ቤቶች እና 4 ቅርንጫፎች በጸጥታ ምክንያት ኦዲቱ ተጀምሮ የተቋረጠ ሲሆን 1መ/ቤት ቢሮ ባለማቅረቡ አፈጻጸሙም የ151 መ/ቤቶች፤ አንድ የተጠቃለለ የመንግስት ሂሳብ እና 54 ቅርንጫፎች ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርቱ ወጪ የተደረገ ሲሆን ባጠቃላይ የመንግሰት ሂሳብ ኦዲትን ጨምሮ 94.44% መፈጸም ተችሏል።

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በተከናወነባቸው መ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫ ላይ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች፣

13.የ2015 በጀት ዓመት የኦዲት አስተያየት ከ2013 እና 2014 በጀት ሂሳብ ኦዲት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መግለጫ /የተሰጠው የኦዲት አስተያየት/	ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት		
	2013	2014	2015
ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት	51	73	79
ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው የተገኙ	73	65	50
አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች	8	6	7
የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው	39	20	15
በፀጥታ ምክንያት ኦዲቱ ያልተሰራ	4	1	10
የመውጫ ስብሳባ ያልተካሄደባቸውና ለስራ አመራር ሪፖርት ምላሽ ያሰጡ በመሆኑ በዚህ ሪፖርት ያልተካተቱ	2		
ሂሳባቸውን በወቅቱ ስላልዘጉ ኦዲት ያልተደረጉ	1		
ቢሮ ባለመስጠት ኦዲት ያልተደረጉ	1		1
ድምር	**179**	**165**	**162**

1. <u>የጥሬ ገንዘብ ጉድለት</u>

14.በጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ላይ ተገቢ ዉ ቁጥጥር እና ክትትል የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ2 መ/ቤቶች **ብር 383,238.48** የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡

15.በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ እንዲተካ እንዲሁም የተሰጣቸውን ሃላፊነት በአግባቡ ያልተወጡ ሰራተኞች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

2. <u>ዉዝፍ የተሰብሳቢ ሂሳብ፤</u>

16.በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እስከ 35 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 እና 5/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ እንዲሁም ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት መወራረድ እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ በ124 መ/ቤቶች በጠቅላላው **ብር 14,119,163,104.23** በወቅቱ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡

17.በወቅቱ ያልተሰበሰበው ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን፤ ከአንድ ወር በላይ እስከ አንድ ዓመት **ብር 1,193,674,117.88፣** ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት **ብር 10,957,913,180.42** ፤ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት **ብር 1,722,681,309.82** እና ከአሥር ዓመት በላይ **ብር 139,093,398.22** ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 105,801,097.89 በቆይታ ጊዜው ያልተተነተነ ነው፡፡

18.ውዝፍ ተሰብሳቢ ሒሳብ ከተገኘባቸው ተቋማት መካከል ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት ጤና ሚኒስቴር **ብር 6,005,511,975.43፣** የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር **ብር 1,159,744,049.53፣** የትምህርት ሚኒስቴር **ብር 1,012,583,714.10፣** በፌዴራል መንግስት ህንፃዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት **ብር 970,941,401፣** የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም የህክምና ኮሌጅ **ብር 756,353,005.50፣** የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ **ብር 433,597,818.50፣** የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት **ብር 286,886,896.20፣** የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን **ብር 272,499,071.20፣** የመንግስት ግዥ አገልግሎት **ብር 265,228,072.78፣** የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን**ብር 250,766,953.97** እና የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር **ብር** 218,363,536.20 ዋና ዋናዎች ናቸው፡፡

19.በተጨማሪም የፕሮጀክት ሂሳብ ባየንባቸው 4 መ/ቤቶች ብር 514,525,280.43 በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

20.የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 /4 ፊደል መ የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁንና በ15 መ/ቤቶች በጠቅላላው ብር 363,101,215.10 ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ ታዉቋል፡

21.የተሰብሳቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለባቸዉ መ/ቤቶች መካከል የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 253,373,189.31፣ የመንግስት ግዥ አገልግሎት 39,163,790.17 እና የጤና ሚኒስቴር 28,002,059.43 ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል፡፡

22.በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብን በወቅቱ አለማወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መባከን በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲሰበሰብ ወይም እንዲወራረድ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ማስረጃ ያልቀረበለት ተሰብሳቢ ማስረጃው እንዲቀርብ በማድረግ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

3. <u>የገቢ ሂሳብ፤</u>

3.1. <u>በገቢ ግብር ቀረጥ እና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ ለመሰባሰብ በሚደነግጉ አዋጆች ደንብ እና መመሪያዎች መሰረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሳብ</u>

23.የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆችና ደንቦች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

24. በገቢዎች ሚ/ር እና በጉምሩክ ኮሚሽን ስር ባሉ 20 ቅርንጫፍ ጸ/ቤቶች በተለያየ ደረጃ የሚገኝ መሰብሰብ ያለበት ያልተሰበሰበ የገቢ ሂሳብ በድምሩ ብር 6,423,974,231.19 ያልተሰበሰበ ሲሆን በሌሎች መ/ቤቶች ደግሞ ከተከፋይ ላይ

ቆርጠው ለገቢ ሰብሳቢው ገቢ ባለማድረጋቸው ያልተሰበሰበ የገቢ ሂሳብ ብር 14,613,015.45 ያልተሰበሰበ መሆኑ በኦዲቱ ታዉቋዋል፡፡

25.ገቢው ያልተሰበሰበት ምክንያት በኦዲት ወቅት በታዩት ክፍተቶች፡- በድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ዉሳኔ መሰረት በወቅቱ ባለመሰብሰቡ፣ ቅሬታ የቀረበበት ዉሳኔ ሳይሰጠው በመዘግየቱ፣ በተክክለኛው ታሪፍ ባለማስከፈል፣ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መካተት ያለባቸው ወጭዎች ባለመካተታቸው፣ በወቅቱ የምንዛሬ መጠን ባለመሰላቱ፣ ከቀረጥ ነጻ የገባ ጥሬ እቃ በግዜ ገደቡ ምርት ላይ ባለማዋሉ እና ለዉጭ ገበያ ባለማቅረቡ አስቀድሞ በቫዉቸር የተመዘገበው ቀረጥ እና ታክሱ ባለመሰብሰቡ፣ ከማህበራዊ ልማት ቀረጥ መሰብሰብ ያለበት ባለመሰብሰቡ በተጨማሪም የስራ ግብር የተጨማሪ እሴት ታክስ የቅድመ-ግብር ክፍያ ተቀንሶ ለገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት ገቢ ባለመደረጉ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

3.2. <u>ያልተሰበሰበ ዉዝፍ የገቢ ሂሳብ</u>

26.በገቢዎች ሚኒስቴር በሚገኙ 9 ቅርንጫፎች እና በጉምሩክ ኮሚሽን ስር በሚገኙ 11 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በተለያየ ደረጃ የሚገኝ እስከ ሰባት አመት የሚደርስ በድምሩ ብር 13,235,504,209.58 ተሰብሰቢ ዉዝፍ የገቢ ሂሳብ እንደሚገኝ በ2014 በጀት ዓመት ሪፖርት ተመላክቷል። ነገር ግን በተሰጠው ማሻሻያ ሃሳብ መሰረት እርምጃ እንዳልተወሰደ ታውቋል።

27. በመሆኑም በተሰጡ የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰዱ ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ሪፖርት እንዲቀርብ አሳስበናል፡፡ እንዲሁም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት የሚያከናውናቸውን ማህበራዊ እና የኢኮኖሚ ልማት አገልግሎቶችን ለማስፋፋት ወሳኝ በመሆኑ የገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲሰራ ያልተሰበሰበዉ ዉዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል።

3.3. <u>ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ እና የስራ ግብር</u>

28.የውል ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው መሰብስብ የሚገባው የጉዳት ካሳ በ5 መ/ቤቶች እና ሶስት ቅርንጫፎች ብር 1,017,192.80 አለመሰብሰቡ ታውቋል፡፡ እንዲሁም ተቀናሽ መደረግ የነበረበት ብር 26,521,701.84 የሥራ ግብር በአንድ መ/ቤት እንዲቀነስ አለመደረጉ ተረጋግጧል፡፡

29.በተገባው ውል መሰረት የጉዳት ካሳ እንዲሰበሰብ እና በመመሪያው መሰረት ተገቢው የሥራ ግብር ተቀንሶ ገቢ መደረግ እንዳለበት በላክነዉ ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4. ለትምህርት ከተላኩ ያልተሰበሰበ

30.በመንግሰት ወጪ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጪ ሀገር ተልከው ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ አገራቸው ተመልሰው በውላቸው መሰረት ለመንግስት አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ4 ዩኒቨርስቲዎች እና በ2 መ/ቤቶች በውሉ መሰረት ባለመፈጸማቸው ብር 14,263,345.98 ተመላሽ/ገቢ ያልተደረገ ሂሳብ በኦዲት ተገኝቷል፡፡

31.በውላቸው መሰረት ያላስመለሱ ጅግጅጋ ዩኒቨርሰቲ ብር 4,034,214.00፣ ዲላ ዩኒቨርሰቲ ብር 2,945,762.00፣ አምቦ ዩኒቨርስቲ ብር 2,232,043.78፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ብር 2,232,043.78 እና ጤና ሚ/ር ብር 1,869,744.20 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

32.በመሆኑም መ/ቤቶቹ በውላቸው መሰረት ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ሊያደርጉ እና ካልሆንም ገንዘቡን በዉሉ መሰረት እንዲያስመልሱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

3.5. ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ፣

33.የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ2 መ/ቤቶች ከተለያዩ የገቢ ማመንጫ የተሰበሰበው ገቢ ብር 910,656.04 በገቢዎች ሚ/ር ስር ባሉ 6 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 8,064,290.11 በድምሩ ብር 8,974,946.15 የገቢ ሂሳቡን ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም። እንዲሁም በኢምግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት በዶላር የተሰበሰበውን 1,374,914 ገቢ የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

34.ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.6. በመንግስት የጸደቀ የማስከፈያ የዋጋ ተመን (ታሪፍ) ሳይኖር የተሰበሰበ

35.የመንግስት መ/ቤቶች ከተለያየ አገልግሎቶች የሚሰበስቡት ገቢ በመንግስት በጸደቀ የዋጋ ተመን መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡- በ8 መ/ቤቶች በመንግስት የጸደቀ የማስከፈያ የዋጋ ተመን /ታሪፍ ሳይኖር ብር 187,189,294.74፣ የተሰበሰበ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

36.በመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ እና መመሪያ መሰረት በጥናት እና በመረጃ የተደገፈ የዋጋ ማስከፈያ ተመን በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል አቅርበው በማጸደቅ ገቢ እንዲሰበስቡ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4. የወጪ ሂሳብ፣

37.መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሰረት በአግባቡ ወጪ ማድረጋቸውን፣ መጠቀማቸውን ተገቢውን ማስረጃ መቅረቡን እና ሂሳቡም በትክክል መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለካቱት ግኝቶች ተገኝቷል፡፡

4.1. ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፣

4.1.1. ምንም አይነት ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ

38.በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ11 መ/ቤቶች ብር 43,545,036.91 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ የተመዘገበና ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣

39.ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 17,474,125.03፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ብር 8,794,834.49፣ የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ብር 8,746,697.81፣ የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,406,764.60 እና የኢትዮጵያ አካል ድጋፍ አገልግሎት ብር 3,325,475.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

40.ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.1.2. የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ

41.በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ48 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 44,540,734.65 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

42. የተሟላ ማስረጃ ሳይዙ ወጪን ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል ማዕድን ሚኒስቴር ብር 5,719,611.76፣ ጅግጂጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,716,485.82፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 4,677,134.45፣ የገንዘብ ሚኒስቴር ብር 3,034,625.64፣ በሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ገዋኔ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ኮሌጅ ብር 2,455,915.5 እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ብር 2,185,589.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

43. ለክፍያዎች የወጪ ማስረጃ የማይቀርብላቸው ከሆነ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ካለማስቻሉም በተጨማሪ የወጪ የሂሳቡን ተዓማኒነት ሊያሳጣ የሚችል በመሆኑ የወጪ ማስረጃ ላልቀረበላቸው ክፍያዎች የወጪ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው፤ የወጪ ማስረጃ የማይቀርብላቸው ከሆነ ደግሞ ገንዘቡ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.2. ከደንብና መመሪያ ወጪ አላግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች፣

44. ክፍያዎቹ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ30 መ/ቤቶች ብር 16,407,985.47 ከደንብና መመሪያ ውጭ ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ክፍያ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

45. የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 3,001,220፣ የመንግስት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ብር 2,889,321.58፣ ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ 2,442,200 እና የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,156,500.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

46. መሥሪያ ቤቶች የሚፈጸሚቸው ክፍያዎች በመንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ካልተከተሉ ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በተጨማሪ ክፍያውን ተዓማኒነት ሊያሳጣው እና በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡ ስለሆነም መሥሪያ ቤቶቹ በመንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተከትለው ክፍያ መፈጸም እንዳለባቸው እና አላአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎችም ተመላሽ መደረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.3. በመስሪያ ቤቱ ለሌሉና ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ፣

47.የፌደራል የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ተ.ቁ10 የመንግስት ሰራተኞች የደመወዝ አከፋፈል ደመወዝ ክፍያ ከመፈጸሙ (ወጪ) ከመደረጉ በፊት መከናወን ካለባቸው ጥንቃቄዎች በተለያዩ ምክንያቶች ከስራ የለቀቁ ሰራተኞች ከደመወዝ መክፈያ ዝርዝር መውጣት እንዳለባቸው ይገልጻል በመመሪያ መሠረት ስለመፈጸሙ ኦዲት ሲደረግ፡-

48.በ16 መ/ቤቶች በመስሪያ ቤቱ ለሌሉና ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች **ብር** 485,183.59 ደመወዝ ያላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

49.ክፍያዎች መመሪያን ተከትለው እንዲፈፀሙ ተገቢው ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ እና የተፈጸመው ክፍያም ተመላሽ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡

4.4. አላግባብ የተከፈለ ቅጣት፣

50.በ7 መ/ቤቶች እና በአንድ ቅ/ጽ/ቤት **ብር** 16,346,989.68 አላግባብ የተከፈሉ የተለያዩ ቅጣቶች ተገኝቷል፡፡ አላግባብ ክፍያ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል በጉምሩክ ኮሚሽን የጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት **ብር** 10,070,064.95 (አላግባብ ከመንግስት አካዉንት ለግለሰብ የተከፈለ)፣ የትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን **ብር** 2,960,100.00፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቲያትር **ብር** 1,726,024 እና የኢትዮጵያ ሜትዮሮሎጂ ኢንስትቲዩት 1,501,054.22 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

51.መ/ቤቶቹ መክፈል ያለባቸውን ክፍያዎች በወቅቱ ባለመክፈላቸው መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ የዳረጉትን ሰራተኞች ተገቢዉን እርምጃ እንዲወስዱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

4.5. በብልጫ አላግባብ የተከፈለ ወጪ፣

52.በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ እና መመሪያ የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ32 መ/ቤቶች እና በ9 ቅ/ጽ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች **ብር** 4,968,408.26 እና ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች **ብር** 57,683,793.41 በድምሩ **ብር** 62,683,793.41 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

53.በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱንና የወጡትን ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው፣ በብልጫ የተከፈለውም ገንዘብ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.6. የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች፣

54. የዕቃና አገልግሎት ግዥዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በ73 መ/ቤቶችና በ15 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 2,199,202,363.76 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

55. ከዚህ ዉስጥ በጨረታ መገዛት ሲገባው ያለጨረታ በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ ብር 1,846,143,783.17፣ መስፈርቱን ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተገዛ ብር 104,357,572.10፣ ግልጽ ጨረታ መውጣት ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ ብር 96,187,579.93፣ የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ ብር 13,840,367.55 እና ሌሎች የግዥ ሂደትን ያልተከተሉ ብር 134,673,461.01 ናቸው፡ ከግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፡-

56. ገቢዎች ሚኒስቴር ዋናው መ/ቤት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ብር 1,499,176,626.66፣ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ብር 91,059,356.22፣ የውሀና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 65,505,288.81፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 62,911,764.97፣ የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ብር 57,185,359.91፣ ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ብር 37,430,081.28፣ በጉምሩክ ኮሚሽን በዋናው መ/ቤት እና በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ብር 34,025,491.02 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

57. በመሆኑም ለወደፊቱ ግዥዎች ሲፈፀሙ መንግሥት ባወጣው የግዥ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፣ የመንግስትን አዋጅ በማያከብሩ መ/ቤቶች ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.7. በናሙና መሰረት ገቢ ለመሆኑ በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ የተፈጸሙ ክፍያዎች፣

58. እቃው ወይም አገልግሎቱ በተፈለገ ባህሪያት ዝርዝር መሰረት መቅረቡን ወይም አገልግሎት ለመሰጠቱ በሚመለከተው አካል (ክፍል) መረጋገጡ ኦዲት ሲደረግ በ14 መ/ቤቶች ብር 96,429,644.41 የተገዙ እቃዎች በተፈላጊ ባህሪያቸው ሳይረጋገጥ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ ተረጋግጧል።

59. ማንኛውንም የዕቃ ግዥ ተፈጽሞ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ከመደረጉ በፊት በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር (Specification) መሰረት ተገዝቶ ለመቅረቡ በቴክኒክ ኮሚቴ (በባለሙያ) ወይም አገልግሎት ለመስጠቱ በሚመለከተው አካል (ክፍል) መረጋገጥ

ስላለበት ለወደፊቱ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት እንዲያረጋግጡ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.8. የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት፣

60.በመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተገዛ ንብረት ለመ/ቤቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ9 መ/ቤቶች በድምሩ **ብር** 2,196,501.19 ንብረቱ ገቢ ስለመሆኑ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል።

61.በተጨማሪም ቀረጥ እና ታክስ የተከፈለባቸው ንብረቶች ገቢ መደረግ ሲኖርባቸው በኢትዮጵያ ሜትዮሮሎጂ ኢንስቲቲዩት **ብር** 57,923,136.20 እና በኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲቲዩት **ብር** 730,018.93 በድምሩ **ብር** 58,653,155.12 ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን የንብረት ገቢ ማስረጃ አልቀረበም።

62.ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጣው ገንዘብ ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ መንግስት ላወጣው ወጪ ተመጣጠኝ አገልግሎት ስለመግኘቱ ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን የተገዛው ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

63. በመሆኑም መ/ቤቶች ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ እና ጥቅም ላይ ለማዋላቸው ተረጋግጦ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ የንብረት ደረሰኝ እንዲቀርብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.9. በአማካሪ መሃንዲስ ሳይረጋገጥ የተከፈለ ክፍያ፣

64.የግንባታ ክፍያዎች በአማካሪ መሃንዲ እየተረጋገጠ መከፈሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ2 መ/ቤቶች በድምሩ **ብር** 170,394,448.47 በአማካሪ መሃንዲስ የክፍያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይቀርብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ በዚህ መልኩ ክፍያ ከፈጸሙ ተቋማት መካከል የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚ/ር **ብር** 169,777,652.20 በመክፈል ትልቁን ድርሻ ይዟል።

65.ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት በአማካሪ መሃንዲስ እየተረጋገጠ እና የክፍያ የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቀርቦ መፈጸም እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

4.10. <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፣</u>

66.በበጀት ዓመቱ በመንግስት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያን ተከትሎ የተፈፀመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ4 መ/ቤቶች በድምሩ **ብር** 7,016,570.32 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዘግቦ ተገኝቷል፡፡

67.የመንግስት ሂሳብ አያያዝ ስርዓት በሚያዝዘው መሰረት የሂሳብ ማስተካከያ በመስራት የቅድሚያ ክፍያው በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ እና ለወደፊቱም የሂሳብ ምዝገባ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲፈጸም ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.11. <u>የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ፣</u>

68.የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ74 መ/ቤቶች በድምሩ **ብር** 293,470,433.15 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሳይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡

69.በመሆኑም ለወደፊቱ ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5. <u>የተከፋይ ሂሣብ፣</u>

5.1. <u>በወቅቱ ያለተከፈለ ዉዝፍ ተከፋይ ሂሳብ፣</u>

70.በገንዘብ ሚኒስቴር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ81 መ/ቤቶች **ብር** 1,052,366,599.87 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ የተከፋይ ሂሳቡ በዕድሜ ቆይታ ጊዜው ሲተነተን፡- ከአንድ ወር በላይ እስከ አንድ ዓመት **ብር** 226,938,553.05፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት **ብር** 508,975,623.31፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት **ብር** 29,599,360.42 እና ከአሥር ዓመት በላይ **ብር** 284,952,444.76 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ **ብር** 1,900,618.33 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ያልተለየ ሂሳብ ነው፡፡ በተጨማሪም በ4 መ/ቤቶች ደግሞ ከአንድ ወር አስከ አስር ዓመት የቆየ በድምሩ **ብር** 23,994,403.12 የፕሮጀክት ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ በኦዲቱ ታይቷል፡፡

71. በተጨማሪም ተከፋይ ሂሳብ ላይ ማጣራት ሲደረግ በ14 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 1,754,048,466.57 በተከፋይ ተይዞ የሚገኝ ሲሆን ለማን እንደሚከፈል ተለይቶ የማይታወቅ መሆኑ ታዉቋል። የተከፋይ ሂሳብ ባለመብት መለየት ካልቻሉ መ/ቤቶች መካከል የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር ብር 1,547,886,590.23፣ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚ/ር ብር 131,833,508.57 እና ማዕድን ሚ/ር ብር 29,942,254.79 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

72. ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ለባለ መብቱ ካልተከፈለ የመንግስትን እዳ ከፍ ብሎ እንዲታይ ስለሚያደረግ መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለባለመብቱ የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው ትክክለኛ የመ/ቤቱ ዕዳ መሆኑን በማጣራት ክፍያ እንዲፈጽሙ ወይም ተገቢውን ማስተካከያ እንዲያደርጉ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

6. የበጀት አጠቃቀም፣

73. ኦዲት በተደረገባቸው መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

6.1. ለበጀት ኮዱ ከተደለደለው በላይ የወጣ፣

74. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በ20 መ/ቤቶች በልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ለእያንዳንዱ የበጀት ኮድ ከተደለደለው በላይ ወጪ የሆነ ሂሳብ ከመደበኛ በጀት ብር 524,796,213.55፣ ከውስጥ ገቢ ብር 288,998,079.52 እና ከካፒታል በጀት ብር 489,429,895.62 በድምሩ ብር 1,303,224,188.69 ተገኝቷል፡፡

75. በኮድ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች መካከል፡- የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 322,547,520.30፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና ተጠሪ ተቋማቱ ብር 267,930,274.60፣ የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 173,212,241.40፣ የወለጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 128,153,771.30፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ብር 109,533,570.54፣ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 91,376,175.48፣ የአምቦ ዩኒቨርስቲ ብር 83,386,864.29 እና የአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ 75,107,915.65 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

76. ከዚህ በተጨማሪም በ2 መ/ቤቶች ብር 9,741,854.73 በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ወይም ሳይፈቀድ የተፈፀሙ ክፍያዎች መኖራቸው ታዉቋል።

77. መ/ቤቶች በበጀት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉ እንደሚገባ እና የበጀት እጥረት ካጋጠመም በበጀት ሕጉ መሰረት የበጀት ዝውውር መጠየቅ እንዳለባቸው በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

6.2. ያልተሰራበት በጀት፣

78. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ መጠቀማቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% በላይ ያልተጠቀሙበትን ብቻ በመውሰድ በ101 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 5,357,361,315.89፣ በውስጥ ገቢ ብር 207,644,481.79 እና ካፒታል ብር 13,725,126,257.26 በድምሩ ብር 19,290,132,054.94 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል።

79. የተደለደለው በጀት ስራ ላይ እንዲውል ካላደረጉ መ/ቤቶች መ/ቤቶች መካከል፡- የገንዘብ ሚኒስቴር ብር 8,018,899,476.47፣ ጤና ሚኒስቴር ብር 1,993,400,893፣ የግብርና ሚኒስቴር ብር 1,202,273,994፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 818,498,803.75፣ የወለጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 727,839,708.80፣ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 724,283,117.70፣ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 613,657,992.10፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

80. በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም የታቀዱ ሥራዎች ሳይከናወኑ ሊቀሩና መ/ቤቱም ዓላማውን እንዳያሳካ ሊያደርግ ስለሚችል፣ ለወደፊቱ በበጀት ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ፣

7.1. የንብረት አያያዝ እና አጠባበቅ በተመለከተ፣

81. መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች መኖራቸውን በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡

ንብረት አስተዳደር

የግኝት መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	15	1
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	9	4
ዓመታዊ የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	14	
ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ/ስቶር ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	6	3
የአላቂ የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ	21	2
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	44	3
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግስት መመሪያ መሰረት ሳይወደጉ የተገኘባቸው	56	8
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሰራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	15	
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) ያላዘጋጁ	10	2
የንብረት ክፍል ሰራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ያልተረጋገጠ	3	
የንብረት ጥበቃ ላይ ተመድበው ተያዥ/ዋስትና ያላቀረቡ ሰራተኞች	1	
በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ንብረቶች አያያዝ ችግር የሚታይባቸውና ዓመታዊ ቆጠራ ያልተደረጉ		6
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙባቸው የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ ያላደረጉ	15	3
በእርዳታና በስጦታ ለተገኙ ዕቃዎቾ ዋጋ ያልተመኑ	1	2
አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ ዕቃዎች ተለይተው የማይቀመጡ መሆኑ		6
ጊዜው ያለፈበት መድሃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ	15	1

82. መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለብልሽት እና ብክነት የመጋለጥ እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡

83. የእነዚህ የተለያዩ የንብረት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው በእያንዳንዱ የኦዲት ሪፖርት በዝርዝር እና ዋና ዋናዎቹም በየዘርፉ የንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ ሌሎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች በሚል ተገልጿል።

84.በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፣ አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንና ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችና ኬሚካሎች በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረትና በጥንቃቄ እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7.2. የተሽከርካሪ አጠቃቀም እና አያያዝ፣

85.የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ

የግኝት መግለጫ	የተሽከርካሪዎች ብዛት		
	የመ/ቤቶች/ቅ*	መኪና	ሞተር ብስክሌቶች/**
ሊብሬ ያልቀረበላቸው	13/3*	85	11/6**
በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የቆሙ	37/4*	473	27/65**
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው	2/2*	5	11
የባሌቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መ/ቤቶችና ድርጅቶች ስም የሆነ	21/4*	188	20
የሞተር ቁጥር የሌላቸው	1	5	4
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት ያለው	1	8	
የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው /ጌጅ/ የማይሰራ	9	85	4
የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው / ያላደራጁ	10/1*	89	4
ሊብሬው ብቻ ኖሮ ተሽከርካሪው በአካል የሌለ	1/1*	1	4

ቅ*- ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ** ሌሎች- ሎቤድ፣ትራክተር፣ የቁፋሮ ማሽን

86.በመሆኑም መ/ቤቶቹ ግኝቱ ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ፣ የማያገለግሉት እና የቆሙት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳዳር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ/እንዲወገዱ፣ ሊብሬ እና ሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው እንዲወጣላቸው አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

8. የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስከበር ፕሮጀክት ኦዲት፣

87. የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲት የአገልግሎቱ አቅራቢ በሆኑ በወረዳና በክልል ደረጃ በሚገኙ የጤና ፣የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሃብት፣ የንፁህ ውሃ አቅርቦትና የገጠር መንገድ ሴክተሮች እየተከናወነ በስምምነቱ መሰረት የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ፣ የማረጋገጫ ኦዲት ደግሞ በገንዘብ ሚኒስቴር በተጠየቀ ጊዜ እየተሳራ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ተደርጓል፡

88. በዚሁ መሰረት በበጀት ዓመቱ 313 የተከታታይ፣ 23 የማረጋገጫ (Verification) እና 1 ዓመታዊ ማጠቃለያ ጠቅላላ ድምር 337 ኦዲቶችን ለመሥራት የታቀደ ሲሆን በበጀት ዓመቱ አፈጻጸሙም ሲታይ 320 የተከታታይ ኦዲት፣ 24 የማረጋገጫ (Verification)፣ 1 ዓመታዊ ማጠቃለያ በጠቅላላ ድምር 345 (102.37%%) ኦዲቶችን ማከናወን ተችሏል፡፡

9. የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲትን በተመለከተ፣

89. በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከገንዘብ ሚኒስቴር በተላከው የ2015 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት በመስጠት የገቢና ወጪ፣ ሀብትና ዕዳ እንዲሁም የመንግሥት ገንዘብ ነክ የሆኑ መረጃዎችን ኦዲት በማድረግ ሪፖርቱ ማቅረብ እንዳለበት ይጠቅሳል በዚሁ መሰረትም ሪፖርቱ ተሰርቶ ለሚመለከታቸዉ አካላት ተልኳል፡፡

10. የልዩ ኦዲት ስራዎች፣

90. በበጀት አመቱ ካለን የሰው ሃይል አንጻር በእቅድ ለመስራት የተያዘዉ 11 የልዩ ኦዲት ስራ ቢሆንም የልዩ ኦዲት በበጀት አመቱ 26 ኦዲት ይደረግልን ጥያቄ በመቅረቡ የመደበኛ ኦዲት ዳይሬክቶሬቶችን ጨምሮ በማሳተፍ 23 የልዩ ኦዲት ማከናወን ተችሏል፡፡ የተሰራው የኦዲት ሪፖርትም ለሚመለከታቸው እና ኦዲቱ እንዲሰራላቸው ለጠየቁ አካላት እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡

11. የፌደራል መንግስት ለክልሎች የሰጠውን ድጋፍ እና ድጎማ በጀት የኦዲት ሪፖርት በተመለከተ፣

91.የፌዴራል መንግስቱ ለክልል መንግስታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎችን ኦዲት የማድረግ ሥልጣን በህገመንግስቱ አንቀጽ 94/2 እና በአዋጅ ቁጥር 982/2008 እንደተሻሻለው 1146/2011 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 16 ለፌዴራል ዋና ኦዲተር የተሰጠ እና ለክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶችም በክልሎቻቸው ተመሳሳይ ስልጣንና ኃላፊነት የተሰጣቸው በመሆኑ ይህን የውጭ ኦዲት ድግግሞሽን ለማስቀረት የነጠላ ኦዲት አዋጅ ቁጥር 1251/2013 እንዲወጣ ተደርጓል።

ይህን መሰረት በማድረግ የአፈጻጸም መመሪያ በማዉጣት በ2014 በጀት አመት በአራት ክልል ብቻ ተጀምሮ የነበረዉን በማስፋት በ2015 በጀት ዓመት በ12 ክልሎች እና በሁለት ከተማ አስተዳደር የፌደራሉ መንግስት ለክልል መንግስታት የበጀት እና ልዩ ድጎማዎች ኦዲትን ለማከናወን ሃዋሳ በተካሄደዉ 22ኛው የዋና ኦዲተሮች እና የባለድርሻ አካላት ጉባኤ ላይ ስምምነት ተደርሷል፡፡

92.በዚሁ መሰረት የክልል ዋና ኦዲተሮች በተሰጣቸው ውክልና መሰረት በኦሮሚያ ክልል 326 መ/ቤቶች፣ በአማራ ክልል 67 ፣ ሲዳማ ክልል 36፣ ሶማሌ ክልል 6፣ ሐረሪ ክልል 7፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 13፣ የደቡብ ምዕራብ ክልል 9፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል 25፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል 17፣ የድሬደዋ ከተማ አስተዳድር 14 መ/ቤቶች እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 15 ፕሮጀክቶች ላይ በበጀት መጠን በአጠቃላይ **ብር 188,886,143,079.95** በነጠላ ኦዲት ሽፋን እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ በኦዲት ግኝቶች ላይ የታዩትን ክፍተቶች በተሰጠው አስተያየት መሰረት አሰፈላጊውን ማሻሻያ እንዲያደርጉ በሪፖርቱ አሳስበናል፡፡

የተከበሩ አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ የመንግስት ወጪ አስተዳደር ቁ/ጉ/ቋ/ኮ/ሰብሳቢ!

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

<u>የክዋኔ ኦዲት አፈጻጸምና ዋና ዋና ግኝቶችን በተመለከተ፣</u>

1. መ/ቤታችን ከፋይናንስና የሕጋዊነት (Regularity) ኦዲት በተጨማሪ በክዋኔ ኦዲት ላይ ትኩረት ለማድረግ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በሶስት የክዋኔ ኦዲት ዳይሬክቶሬት እና አንድ የአካባቢ ኦዲት ዳይረክቶሬት በድምሩ በ4 ዳይሬክቶሬት 32 ቡድን በማደራጀት በመንግሥት መ/ቤቶች የ10 አመቱን መሪ እቅድ ለማሳካት የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች፣ እንዲሁም ለተልዕኮ ማስፈፀሚያ የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ ማሳካታቸውን እና የአካባቢ ጥበቃና የዘላቂ ልማት ግቦችን ሊያሳካ በሚችል መልኩ ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ የካቲት 2015 ተጀምረው እስከ ጥር 30/2016 የሚጠናቀቁ 32 አዳዲስ የክዋኔ እና አከባቢ ኦዲቶች እና 12 የክትትል ኦዲቶችን በድምሩ 44 ኦዲቶችን ለማከናወን እቅድ ተይዘው ነበር፡

2. በዚሁ መሰረትም 32 አዲስ ክዋኔ እና አከባቢ ኦዲቶች እና 11 የክትትል ኦዲቶች በድምሩ የ43 ክዋኔ እና አከባቢ ኦዲቶች የተሰሩ ሲሆን አንድ የክትትል ኦዲት በሰዉ ኃይል እጥረት ምክንያት ያልተሰራ በመሆኑ አፈጻጸሙ ከዕቅድ አንጻር በመቶኛ 97.72% ሆኗል።

   ከ2014/15 በጀት አመት ጋር ሲነጻጸር 11 የክዋኔ ኦዲቶችን በመጨመር ሽፋኑ ከነበረበት በ34%እንዲጨምር ተደርጓል፡፡ ኦዲታቸው ተጠናቆ ሪፖርታቸው ለም/ቤቱና ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡

   ከተሰሩት የክዋኔ ኦዲቶች ዉስጥ 7ቱ የአካባቢ ኦዲቶች ሲሆኑ ሌሎቹ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በዘላቂ ልማት ግቦች እንዲሁም በሴቶች አሳታፊነት እና ተጠቃሚነት ላይ ያተኮሩ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

በዚህ አመት ከሌላው ግዜ በተለየ ሁኔታ በሁሉም የክዋኔ እና አከባቢ ኦዲቶች ላይ የባለ ዘርፈ-ብዙ ጉዳዮችን በመመዘኛ መስፈርት በማካተት የተሰራ ሲሆን በተጨማሪም በምክር ቤቱ እንዲሰሩ የተጠየቁ 2 የክዋኔ ኦዲቶችም እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ በዚህም አግባብ የምክር ቤቱን ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

<u>በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የፕሮጀክት ውል እና የሰው ኃብት አስተዳደርን በተመለከተ፣</u>

ኦዲቱ የተከናወነው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በቀረበ ጥያቄ ነው፡፡

3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሚያከናውናቸው የተለያዩ ፕሮጀክቶች ችግር ፈቺ እና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ፕሮጀክቶች ከመቀረጻቸው በፊት የሀገሪቱን እና የማህበረሰቡን የቴክኖሎጂ ፍላጎት እና ክፍተት መሰረት ያደረገ ጥናት (Need assessment) በማዘጋጀት ግምገማ ማድረግ ሲኖርበት ጥናት ያልተደረገባቸው ፕሮጀክቶች መኖራቸው፤
4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፕሮጀክቶች የሚያስፈልጉ ግዥዎች በግዥ መመሪያ መሰረት ግዥ ያልፈጸመ መሆኑ እንዲሁም በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ፕሮጀክት የመኪና ኪራይ አገልግሎት ከተገባው ውል ውጭ **ብር** 3,925,055.80 ያለ አግባብ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
5. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች በተገባው ውል እና ዕቅድ መሰረት እንዲጠናቀቁ ባለማድረጉ መንግሰትን ለተጨማሪ ወጪ የዳረገው መሆኑ፣
   ለማሳያም፡
   - ✓ ሞዴል የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቤተ-መጽሀፍት (ሳይንስ ካፌ) በተያዘለት ጊዜ እና በጀት ባለመጠናቀቁ ሚ/ር መ/ቤቱ **ብር** 43,044,953.22 ለተጨማሪ ወጪ መዳረጉ፤
   - ✓ ነባሩን ዳታ ማዕከል ማሻሻል ፕሮጀክት በተያዘለት ጊዜ እና በጀት ባለመጠናቀቁ **ብር** 277,071,644.36 ለተጨማሪ ወጪ የተዳረገ መሆኑ፤
   - ✓ እንዲሁም የፕሮጀክት ክትትል እና ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ የፕሮጀክት አፈጻጸም ክትትል ስራን በዕቅድ በመያዝ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤
6. የሞዴል የሳይንስና ቴክኖሎጂ ማዕከል (የሳይንስ ካፌ) ፕሮጀክት ወጣቶች በሚቋቋሙ ማዕከላት የሳይንስ፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ እውቀት እንዲያዳብሩ፣ እንዲሁም የተለያዩ ይዘት ያላቸው የዲጂታል ቤተ-መጽሀፍ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ ፕሮጀክት ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያቋቋማቸው 5 የሳይንስ ካፌ ማዕከላት ከታለመላቸው አላማ ውጭ ማለትም የካፍቴሪያ አገልግሎት፣ የፑል መጫወቻ፣ ፕሌይ ስቴሽን እና ለስፖርት ማዘውተሪያ እንዲውሉ የተደረገ መሆኑ፤

7. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኦፕን ሶሳይቲ ፋውንዴሽን ድጋፍ ሲተገበር የነበረው የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ፕሮጀክት ላይ በጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት በቀን 10 መጋቢት 2012 ዓ.ም በተዘጋጀው የፕሮጀክት አፈጻጸም ማንዋል ቁጥር 7.4 ላይ የኮንትራት ሰራተኞች ቅጥር በውድድር መፈጸም እንዳለበት ቢገለጸም የቅጥር ማስታወቂያ በማውጣት ፣ የትምህርት እና የስራ ልምድ ማስረጃ እና የመሳሰሉት ተዘጋጅቶ ቅጥር እንዲፈጸም ያልተደረገ መሆኑ፤

8. በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ፕሮጀክት ላይ የቅጥር ውል ሳይኖራቸው እና ውላቸው ለተቋረጠ ስራተኞች የስራ ግብር እና ጡረታ ተቀናንሶ ያለአግባብ አጠቃላይ ብር 2,986,733.31 ደመወዝ የተከፈለ መሆኑ፤ በተጨማሪም በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ፕሮጀክት አፈጻጸም ማንዋል መጋቢት 2012 ዓ.ም ላይ የሰራተኞች ውል ሲሻሻል የደመወዛቸዉን ከ15% በላይ ጭማሪ መደረግ እንደሌለበት ቢገልጽም 4 ሰራተኞች ውል ሲሻሻል የደመወዝ ጭማሪያቸው ከ15% በላይ ማለትም (ከ25-44%) የተጨመረላቸው በመሆኑ በዚህም ብር 645,547 ጭማሪ ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን በጠቅላላ ብር 3,632,280.31 ያለ አግባብ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤

9. በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ፕሮጀክት ላይ የተቀጠሩ ጊዜያዊ ስራተኞች የቅጥር ውላቸው ሲቋረጥ የተረከቡትን ንብረት ያልመለሱ መሆኑ፤ በመሆኑም አጠቃላይ ብር 8,609,114.31 የሚያወጡ የተለያዩ ንብረቶች ወጪ ተደርገው ያልተመለሱ እና እንዲሁም በፕሮጀክቱ የተሰሩ ስራዎች ርክብብ ያልተደረገ መሆኑ፤

10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቶች በተገባው ውል፣ በተያዘላቸው ዕቅድ እና በጀት እንዲጠናቀቁ ለማድረግ የሚያስችል የፕሮጀክቶች ክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ግምገማ ማድረግ እና ግብረ መልስ መስጠት እንዳለበት እንዲሁም ባልተጀመሩ እና በተቋረጡ ፕሮጀክቶች ከመንግስት የሚለቀቀውን በጀት ለታለመለት ዓለማ ለማዋል ፕሮጀክቶቹ የገጠማቸውን ችግር በጥናት በመለየት ወደ ትግበራ እንዲገቡ ማድረግ እንዳለበት በተጨማሪም አላግባብ የተከፈሉ ክፍያዎችም እንዲመለሱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>በወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክትን አፈጻጸምን በተመለከተ</u>፣

በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በህዝብ ውክልና በህዝብ ጥያቄ መሠረት የተሠራ ነው፡፡

11. ለወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ፕሮጀክት ግንባታ የሚውል ወደ ተለያዩ ክልሎች፣ በውጭ ሀገራት በሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽ/ቤቶች በኩል ይሸጣል ተብሎ ተሰራጭቶ ከነበረው ኩፖን የብር መጠኑ ብር 9,388,635.19 የሚያወጣ ኩፖን የጠፋ ሲሆን በተጨማሪም የስራ አመራር ቦርዱ በሀገር ውስጥ ከተሰበሰበ ባንክ ማስገባት የነበረበት ብር 7,705,445. ያልገባ እና ያልተመለሰ ቶምቦላ ብር 20,640.00 ሲሆን በውጭ ሀገራት ለኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽ/ቤቶች ተሰራጭቶ የጠፋ በሚል በአጠቃላይ ብር 17,114,720.19 የእዳ ስረዛ የተደረገ መሆኑ፣

12. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ /የፕሮጀክቱ የስራ አመራር ቦርዱ/ ከዩኒቨርሲቲው ጋር ነሐሴ 24 በ2008 ዓ.ም ባደረጉት የፕሮጀክቱ የርክክብ ስምምነት ላይ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ /የፕሮጀክቱ የስራ አመራር ቦርድ/ ግዴታዎችና ሃላፊነቶች ውስጥ ለፕሮጀክቱ ራሱን የቻለ አንድ ብሎክ /ህንፃ/ ለመገንባት የሚውል ሀብት በማፈላለግ በአገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ተንቀሳቅሶ የፋይናንስ፣ የግንባታ ቁሳቁሶች፣ የህክምና መሳሪያዎችና ሌሎች ሀብቶችን በማሰባሰብ እና ከህብረተሰቡ በተሰበሰበው ገንዘብ የአንድ ብሎክ /ህንፃ/ ግንባታ ወጪ ሙሉ በሙሉ ሸፍኖ በመስራት ለዩኒቨርሲቲው እንደሚያስረክብ በግልፅ ቢቀመጥም ኦዲቱ እስከተከናወነበት ቀን ድረስ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ /የፕሮጀክቱ የስራ አመራር ቦርዱ/ ምንም ዓይነት ህንፃ መገንባት አለመቻሉ፣

13. የወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክትን ህዝባዊነት ለማረጋገጥ፣ አለም አቀፋዊ ስታንዳርዱን የጠበቀ መሆኑን ለመከታተል፣ በየጊዜው የተፈፀሙና ያልተፈፀሙ ተግባራትን በመከታተል ለማስተካከል እና ፕሮጀክቱን ለታለመለት አላማ መዋሉን ማረጋገጥ የሚያስችል ከወሎ ተርሸሪ ኬርና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት የስራ አመራር ቦርድ አባላት፣ ከወሎ ዩኒቨርሲቲ ሥራ አመራር ቦርድ፣ ከህብረተሰቡና ከአካባቢው መስተዳደር የተውጣጣ ከ9-11 አባላት ያሉት የጋራ አማካሪ ቦርድ መቋቋም እንዳለበት ውሳኔ ላይ ቢደረስም ኦዲቱ እስከተከናወነበት ቀን ድረስ የዩኒቨርሲቲው እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የጋራ አማካሪ ቦርዱ ያላቋቋሙ መሆኑ፣

14.የወሎ ተሪሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከህዝብ የተሰበሰበውን ገንዘብና ቁሳቁስ ኦዲት በማስደረግ ሰነዶችን ጨምሮ ለወሎ ዩኒቨርሲቲ እንዲያስረክብ እና ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የስራ ጊዜውን አጠናቆ እንዲዘጋ በ29/09/2010 ዓ.ም ቢወሰንም ኦዲቱ እስከተከናወነበት ቀን ድረስ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በውሳኔው መሰረት የስራ ጊዜውን አጠናቆ አለመዘጋቱ ታውቋል፣

<u>በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሴቶችንና ህፃናትን በተመለከተ በአገሪቱ የተፈረሙ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አፈፃፀምን በተመለከተ፣</u>

15.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሴቶች እና ህፃናት ላይ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በሚፈፀሙ አካላት ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እንዲዘጋጅ በማድረግ ተፈፃሚነቱን ሊከታተልና ሊቆጣጠር የሚገባ ቢሆንም የወንጀለኛ መቅጫ ህግን መሰረት አድርጎ ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች በሚፈፅሙ አካላት ላይ በሚፈለገው ልክ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤ለማሳያም

- ✓ በፖሊስ ጣቢዎች ውስጥ በሴቶች እና በህጻናት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን የተመለከቱ ጉዳዮችን እንዲያስተናግዱ የተቋቋሙ ልዩ የስራ ክፍሎች ሽፋናቸው እና የሎጂስቲክስ አቅማቸው ዝቅተኛ መሆኑ፤
- ✓ ለቤት ውስጥ ጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ ሴቶች የፍትህብሔር መፍትሔዎች አለመኖራቸው፤
- ✓ በፖሊስ አባላት፣ ዐቃቤ ሕጎች እና ዳኞች ዘንድ በሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ ልየታ፣ ምርመራ የመክሰስ እና የፍርድ ሂደት አንጻር የግንዛቤና የማስፈፀም ውስንነቶች መኖራቸው፤
- ✓ በ2011 ዓ.ም ለተባበሩት መንግስታት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ማንኛውም አይነት አድልኦ ለማስወገድ የተቋቋመ ኮሚቴ (CEDAW) በቀረበ በ8ኛ መደበኛ ሪፓርት እንደተገለፀው፤-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ላይ የተቀናጀ ሁሉን አካታች የሆነ ህግ አለመኖር፤በጋብቻ ውስጥ የሚፈፀም አስገድዶ መድፈር ወንጀል ተደርጎ አለመቀመጡ፤

16.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2014 ዓ.ም በአማራ፣ እና በአፋር ክልሎች በጦርነቱ ምክንያት ፆታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች የሚውል ብር 71,145,560 ከመንግስት በጀት በማስመደብ የፀደቀ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ብር 25,969,414.66 ስራ ላይ በማዋል ቀሪው 45,176,145.34 ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤

17. ሴቶች በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ በህገ ወጥ መንገድ የሚዘዋወሩ መሆኑንና በሰው ቤት ሠራተኝነት በሚሰሩበት ጊዜ በቀላሉ ለወሲብ ብዝበዛ የሚጋለጡ መሆኑን የፍትህ ሚኒስቴር በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚፈፀም ጥቃትን ለመከላከል ባዘጋጀው ስትራቴጂክ እቅድ (2016-2020 ዓ.ም) የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ጥናትን (እ.ኤ.አ 2016) እና የህጻናት ፈንድ (UNICEF) ሪፖርትን ጠቅሶ ያስቀመጠ ቢሆንም ለመከላከል የሚያስችል መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ አለመደረጉ፤

18. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለትምህርት የደረሱ ሕፃናት ስብዕናቸውን፣ ተሰጥዖዋቸውን፣ የአዕምሮ እና የአካል ችሎታቸውን በተሟላ መልኩ ለማዳበር የሚረዳ ትምህርት እየተማሩ ስለመሆኑ የሚረጋገጥበት እንዲሁም ሕፃናት ከማንኛውም ትምህርታቸውን ከሚያደናቅፍ፣ ለጤናቸው፣ አካላዊ፣ እና ማህበራዊ እድገታቸው ጎጂ ከሆነ ስራ የተጠበቁ ስለመሆናቸው የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ ታይቷል፤ ስለዚህ ሚ/ር መ/ቤቱ በአለም አቀፍ የተደነገጉ ስምነቶችን ተግባራዊ እንዲያደርግ በላከነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>የማዕድን ሚኒስቴር ከማዕድን የሚገኝ ገቢ ማሳደጉን እና መሰብሰቡን በተመለከተ፣</u>

19. ማዕድን ሚኒስቴር ከተቋቋመ 50 ዓመት በላይ ቢያስቆጥርም ኦዲቱ እስከተከናወነበት ድረስ የማዕድን ሀብትና ልማትን የሚመለከት ፖሊሲ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣

20. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የማዕድን ዘርፉን የሀብት ክምችት በመለየትና የቅድመ አዋጭነት ጥናት በማካሄድ ለመንግስት እና ለግሉ ዘርፍ ኢንቨስትመንት ተደራሽ ሊያደርግ ቢገባዉም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የማዕድን ዘርፉን የሀብት ክምችት በመለየት የቅድመ-አዋጭነት ጥናት ያላጠና መሆኑ፤

21. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገሪቱ የአፈር ማዳበሪያ አለኝታ ክምችት እና ለማዳበሪያ ግብአት የሚሆኑ የካልሼየም፣ ፎስፌት፣ ሰልፈርና ፖታሽ ቦታ በመለየትና የቅድመ አዋጭነት ጥናት በማጥናት ተደራሽ የማድረግ ስራዎች ያልሰራ መሆኑ፤

22. አዲስ እና ነባር የማዕድን መረጃዎችን በዘመናዊ አያያዝ በማደራጀት፣ በህትመት ያሉትን የጥናት ሰነዶች ወደ ዲጂታል በመቀየር ለተጠቃሚዎች በGeospatial database and Portal ተደራሽ የማድረግ ስራ ያልሰራ መሆኑ፤

23. በባሕላዊ መንገድ ወርቅ በሚመረትባቸው ቦታዎች 36 የወርቅ ማጠቢያ ማሽን በማዘጋጀት ማእድኑ በሚገኝባቸው ክልሎች የተሰራጨ እና ስልጠና የተሰጠ ቢሆንም ማሽኖች ስራ ላይ ስለመዋላቸው ክትትል ያላደረገ መሆኑ፤

24. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከማዕድን የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ግኝት በወቅቱ የዶላር ስሌት መሰረት መከናወኑን የማያረጋግጥ መሆኑ፣ ወደ ውጭ የሚላኩ ማዕድናትን የአለም አቀፍ ዋጋን መሰረት በማድረግ የዋጋ ማስተካከያ (ክለሳ) በየጊዜው የማያደርግ መሆኑ፣

25. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኢትዮጵያ ከማዕድን ዘርፍ ከ2010 እሰከ 2016 የመጀመሪያ ሩብ አመት **4.8 ቢሊዮን ዶላር** ለመሰብሰብ በእቅድ ቢያዝም የተሰበሰበዉ **1.9 ቢሊዮን** በመሆኑ የእቅዱን 39% ብቻ በማከናዎኑ ሃገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት ያለባት የዉጭ ምንዛሬ ያላገኘች መሆኑ፣

26. የማዕድን ኢንዱስትሪ ግብዓቶችን እና የማዕድን ውጤቶችን በአገር ውስጥ ለመተካት የድንጋይ ከሰል ለማምረት እና ያመረቱትን ፕሮሰስ ለማድረግ ፈቃድ የተሰጣቸው 9 ኩባንያዎች ወደ ተግባር ያልገቡ መሆኑ፣

27. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለተከታታይ ዓመታት ማለትም ከ2013 ዓ.ም እስከ 2016 ዓ.ም አንደኛ ሩብ አመት ድረስ ከኩባንያ እና ከባህላዊ አምራች ወርቅ አቅራቢዎች የሚገዛው የወርቅ መጠን (በግራም/በባር) ወጥነት የሌለው(ከአመት አመት ዝቅ የሚል) መሆኑ፣

28. በከፍተኛ የማዕድን ማምረት የተሰማራ ባለፍቃድ የመንግስት አክሲዮን ድርሻ ግብር ከከፈለበት ትርፍ ላይ በማስላት በየዓመቱ ለሚመለከተው የመንግስት ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ማድረግ እንዳለበት እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱም ስለመከፈሉ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት በአዋጁ ቢጠቀስም 5% (አምስት በመቶ) የሚሆነውን ነጻ የመንግስት አክስዮን ድርሻ ኩባንያዎች ስለመክፈላቸው የማረጋገጥ ሥራ ያልሰራ እና ክትትል ያላደረገ መሆኑ፣

29. የማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 አንቀፅ 42 ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱን አስቀድሞ በማስፈቀድ ለምርመራ ናሙናዎችን ወደ ውጭ ሀገር ለፍተሻ ቢልክም የናሙና ማዕድናት የመንግስት ንብረት ሆነው ይቆያሉ እንዲሁም ያለማዕድን ሚኒስቴር መ/ቤት ስምምነት ሊሸጥ እንደማይችል ቢገልፅም ለናሙና የሚላኩ ማእድናት ኢኮኖሚክ ጥቅም የላቸውም በማለት ለናሙና ከሄዱ በኋላ የማይመለሱ መሆናቸው፤

30.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እና በዘመናዊ መልክ የተደራጀ ዝርዝር የሥነ-ምድር መረጃ እንዲኖር በማድረግ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ ፕሮሞሽን ዶክመንት በማዘጋጀት አቅምና ልምድ ያላቸውን ባለሀብቶች በመሳብ እንዲሁም የማዕድን ልማቱ ኢንቨስትመንት ከፍ በማድረግ ዘርፉ ለአገር ኢኮኖሚ አስተዋፅኦ እንዲኖረው ማድረግ የሚጠበቅበት መሆኑን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን የፌደራል መንግስት የተቋረጡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በተመለከተ፣

31.በፌዴራል በጀት የሚሰሩ ፕሮጀክቶችን የያዙ ሥራ ተቋራጮች የያዙትን ፕሮጀክት ሳያጠናቅቁ ወይም አፈፃፀማቸው ሳይታይ በሌላ ጨረታ ላይ እንዳይወዳደሩ የሚከለክል የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ቁጥጥርና ክትትል ባለመደረጉ የውል ዋጋቸው በድምሩ **ብር10,764,373,751.02** የሆነ 12 **ፕሮጀክቶች በሁለት ሥራ ተቋራጮች የተያዙ** መሆናቸው፣

32. የፕሮጀክቶች መቋረጥ በመንግስት ሀብት ላይ እየፈጠረ ያለውን ከፍተኛ የገንዘብ ብክነት ሊቀንስ የሚችል ሥራ አስቀድሞ እየተሰራ ባለመሆኑ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ በመጀመሪያ ውለታቸው ሳይጠናቀቁ በሌላ ጨረታ ወደ ግንባታ የገቡ 13 ፕሮጀክቶች በመንግስት ላይ ያስከተሉት ተጨማሪ ወጪ በድምሩ ብር **16,681,131,031.64** መሆኑ፣

33.ባለሥልጣን መ/ቤቱ በውስን ፕሮጀክቶች ክትትልና የቁጥጥር ስራ የጀመረ ቢሆንም ሀገሪቱ በምታከናውነው የፕሮጀክት ልክ የተደራጀና የተቀናጀ የቁጥጥርና ክትትል ሥራ ባለማከናወኑ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ የ38 ፕሮጀክቶች ብር 2,447,202,378.41 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና (Performance Guarantees) በውለታቸው መሰረት ያልተወረሰ/ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፣ እንዲሁም በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ለ25 ፕሮጀክቶች ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ (Advance Payments) **ብር 3,220,090,230.36** ውስጥ፡-**ብር 2,467,795,327.17** ተመላሽ ተደርጎ ለሌሎች የልማት ስራዎች እንዲውል ያልተደረገ መሆኑ፣

34. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ፣ በባህላዊ ቅርሶች፣ በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለመከላከል የሚያስችል ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር እያደረገ ባለመሆኑ በናሙና የታዩ ግንባታ ላይ ባሉ 7 ፕሮጀክቶችን የሚሰሩ ሥራ ተቋራጮች የቅድመ መከላከል ሥራዎችን አሟልተው እየሰሩ አለመሆኑ፤

35. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በጠቅላላ፣ በህንፃ፣ በመንገድ ሥራ እና በልዩ ሥራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ በየደረጃው በመስፈርትነት የተቀመጠውን የሰው ሀይል፣ የተሽከርካሪና ማሽነሪ መጠን በከፊል ሳያሟሉ፣ የማሽነሪ ቴክኒካል ምርመራ ማስረጃ ሳያቀርቡ እና ሳያድሱ፣ የባለሙያዎች የስራ ልምድ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ማስረጃ ሳያቀርቡ፣ የደረጃ ማሻሻያ ሲያደርጉ የድርጅቱን ተርን ኦቨር ማስረጃ ሳያቀርቡ እና የሌላ ሰው መታወቂያ በማቅረብ የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ሥራ ተቋራጮች መኖራቸው፤

36. በመመሪያ ቁጥር 648/13 መሰረት የሥራ ተቋራጭነት ብቃት ማረጋገጫ መሰጠት ያለበት ከደረጃ 1 እስከ 7 ቢሆንም ለ24 ሥራ ተቋራጮች በደረጃ 8 እና 9 መመሪያው በማይፈቅደው ደረጃ የተሰጠ መሆኑ እና ለልዩ ስራ ተቋራጭ የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ዘርፍ እና መመሪያ ላይ የተቀመጠው ዘርፍ የማይመሳሰል መሆኑ፣

37. በጠቅላላ፣ በህንፃ፣ በመንገድ እና በልዩ ሥራ ተቋራጭነት ዘርፍ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው እየተንቀሳቀሱ የሚገኙ 261 የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች እንዳሉ ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተገኘ መረጃ የሚያሳይ ቢሆንም ከ11 ሥራ ተቋራጮች ውጪ በሀገሪቱ የሚንቀሳቀሱ ሁሉንም የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች በምዝገባ መመሪያው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት ቁጥጥርና ክትትል እያደረገ አለመሆኑ፤ ከተመዘገቡት 11 ሥራ ተቋራጮች ውስጥም የተቀመጠውን አነስተኛ መስፈርት ሳያሟሉ የብቃት ማረጋገጫው የተሰጣቸው 3 ስራ ተቋራጮች መኖራቸው፤

38. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ጊዜያቸውን ጠብቀው በማያድሱ ሥራ ተቋራጮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ እርምጃ እየወሰደ ባለመሆኑ በናሙና ከታዩ የ40 ሥራ ተቋራጮች ማህደር ውስጥ 36ቱ ሥራ ተቋራጮች ጊዜያቸውን ጠብቀው ያላደሱ መሆናቸው ታውቋል። ባለስልጣኑ የክትትል እና የቁጥትር ስራዉን ማጠናከር እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የሬዲዮና የቴሌቪዥን የዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ</u>፣

39.የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 1278/2015 አንቀፅ 8/6 መሰረት ቦርዱ የራሱን የአሰራር መመሪያ እንደሚያወጣ ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ ስራዎችን ለመምራት የሚያስችለው የራሱ የሆነ የአሰራር መመሪያ የሌለው እና ያላወጣ መሆኑ፤

40.በሰኔ 2015 ዓ.ም የኢ.ቢ.ሲ ተቋማዊ ሪፎርም የማፅናት ምዕራፍ ሰነድ ላይ እንደተገለጸው ለተፎካካሪ ፓርቲዎች የሚሰጠው ጊዜ አናሳ መሆኑ እንዲሁም የተለየ ሀሳብ ያላቸው የሲቪል ማህበራትና የሙያ ማህበራት ሚዲያው ተገቢ ትኩረት የማይሰጣቸው መሆኑ፣

41.የሬዲዮ የማሰራጫ ጣቢያዎች ካላቸው የማሰራጨት አቅም ከ50% በታች በሆነ መልኩ እያስተላለፉ የሚገኙ መሆኑ እንዲሁም የሬዲዮ የማሰራጫ ጣቢያዎች የመለዋወጫ እቃዎች ሳይገዛ ከ10 አመት በላይ ያስቆጠረ መሆኑ፣

42.የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ ወቅቱን ጠብቆ ስብሰባውን የማያካሂድ መሆኑን፣ እንዲሁም ቦርዱ በ2013 ዓ.ም አንድ (1) ጊዜ ፤ በ2014 ዓ.ም ሶስት(3) ጊዜ እና በ2015 ዓ.ም ደግሞ ሁለት(2) ጊዜ ብቻ የተሰበሰበ መሆኑ፣

43.እንዲሁም በመላ ኢትዮጵያ ድምጾችና ፊልሞች/ቪድዮዎች መቀረጽ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ በኦዲዮ እና በኦድዮቪዥዋል የተቀረጹ ሰነዶች በሙሉ ለማለት በሚቻልበት ሁኔታ የሚገኙት እና ይህ ደግሞ ተቋሙ በድምጽና ፊልም-ቪድዮ ተመዝግቦ የሚገኘውን የአገሪቷን ታሪክ ሙሉ በሙሉ የያዘ ብቸኛ ተቋም መሆኑ በኤዲቶሪያል ፖሊሲው ላይ የተገለፀ ቢሆንም፤ የቴሌቪዥን አርካይቭን እስከ ህዳር 3/3/2016 ዓ.ም ድረስ አስራ አራት ሺህ ሰዓት ብቻ ፋይል ዲጂታላይዝድ የተደረገ እና የቴሌቪዥን አርካይቭ ከአርባ ሺህ ሰዓት በላይ ፋይል ዲጂታላይዝድ ያልተደረገ መሆኑ፣

44.በኮርፖሬሽኑ የ2013-2017ዓ.ም ስትራቴጂክ ዕቅድ ላይ እንደተገለፀው የዲጂታል አርካይቭ ሲሰተም አፕግሬድ በማድረግ ደረጃውን በማሻሻል ተደራሽነቱን በማረጋገጥ እንዲሁም የዲጂታል አርካይቭ ሀብትን ለገቢ ምንጭነት መጠቀም እንዲቻል ቢታቀድም ከተወሰኑ የኒውስ ሩም፤ ኤዲቲንግ ሲስተም ሶፍትዌር ማሻሻያ (upgrade) በስተቀር ሙሉ ለሙሉ በሚፈለገው ደረጃ ያልተከናወነ መሆኑ፣

45.የኢዲቶሪያል ፖሊሲው ከወጣ ከ10 አመት በላይ ቢሆንም ኮርፖሬሽኑ አንድም ጊዜ የሚዲያውን ኢንዱስትሪ እና የአገሪቱን የእድገት ሽግግር ከግምት ውስጥ በማስገባት የኢዲቶሪያል ፖሊሲው ያልከለሰ መሆኑ፣

46.ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች ከሚያሰራጫቸው የዜና ይዘቶች 70% በክልል 30% በማዕከል አድርጎ እየሰራ አለመሆኑንና ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች ከሚያሰራጫቸው ይዘቶች አብዛኛዎቹ ከማዕከል አካባቢ መሆኑ፣ እንዲሁም የቋንቋዎች ዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች ዲቪዥን የሰው ሀይል እና የሚፈልገው ስራ በጣም ሰፊ ልዩነት ያለው መሆኑ እንዲሁም የቋንቋዎች ዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች ዲቪዥን በመዋቅር መሰረት የሚፈልገው የሰው ሀይል ብዛት 244 ሲሆን እስከ የካቲት 2016 ዓ.ም ያለው የሰው ሀይል 81 ብቻ ሲሆን ከተፈቀደው መዋቅር 33% የሚሸፍን መሆኑ፣

47.ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች ከሚያሰራጫቸው ይዘቶች አብዛኛዎች ከማዕከል አካባቢ መሆኑን ማለትም የፌዴራል ዜና የተዘገበው 30 በመቶ መሆን ሲገባው 42.9 በመቶ መሆኑ እና የክልል ዜና 70 በመቶ መሆን ሲገባው 57.1 በመቶ መሆኑ፣

48.የኮርፖሬሽኑ የሬዲዮ ማሰራጫ ኤፍኤም ጣቢያዎች ካሉት 33ቱም ከተማ አካባቢ በመሆኑ ለገጠሩ ነዋሪዎች የሬዲዮ ስርጭት ተደራሽ አለመሆኑ፣ እንዲሁም በተደጋጋሚ ከአድማጭ ተመልካች ግብረ መልስ ሪፖርት ለማወቅ እንደተቻለው ኮርፖሬሽኑ የሬዴዮ ስርጭት ጥራት ችግርና ተደራሽነት ላይ በተደጋጋሚ የህዝብ ቅሬታዎች የሚነሱበት ሲሆን ነገር ግን ኮርፖሬሽኑ ችግርን ለመፍታት ጥረት አለመደረጉ፣

49.ኮርፖሬሽኑ በሚሰራቸው የዜና ዘገባ እቅዶች 30% የሁነት እና 70% የፕሮጀክት የሚለውን መርህ እየተከተለ አለመሆኑ፣ በመጋቢት 27/2015 ዓ.ም በቦርዱ ቃለ ጉባኤ እንደተመለከተው የፕሮጀክት ዜና ሽፋን 60% መድረሱ የተገለፀ ቢሆንም፤ የ2015 ዓ.ም እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ግን በአማርኛ ዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች ከተሰሩት ዜናዎች የፕሮጀክት ዜና ሽፋን 16% እና በቋንቋዎች ዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች ከተሰሩት የፕሮጀክት ዜናዎች ሽፋን 6% መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፤ በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመበትን አለማ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ሃላፊነቱን እንዲወጣ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት አፈፃፀም በተመለከተ፣

50. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶ እና የመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት ለማሳለጥና ተግባራዊ ለማድረግ በተለይ በፍራንኮቫሎታ (የራሳቸው የውጪ ምንዛሬ ያላቸው ዲያስፖራዎች) ሸቀጦችን ወደሃገር እንዲያስገቡ ፈቃድ በተሰጣቸው አስመጪዎች የሚመጡ ሸቀጦች የስርጭት፣ የግብይትና የቁጥጥር ስርዓት ያልተዘረጋላቸው መሆኑ እና ምርቶቹ ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ የስርጭትና የግብይት ሰንሰለቱ የማይታወቅና ቁጥጥር የማይደረግባቸው መሆኑ፤ እንዲሁም የሲሚንቶ መመሪያዎች በግብይቱ ሂደት ላይ ክፍተትን በሚፈታ መልኩ የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ሀገራዊ ጥናት በማካሄድ ሁሉንም አካታች በሆነ መልኩ የማይዘጋጁ መሆኑ፤

51. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የመሰረታዊ ሸቀጦች መጠን/ኮታ 2001 ዓ.ም የተደለደለ ሲሆን ይህ የኮታ ድልድል ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ ክለሳ ያልተደረገበት መሆኑ፤ ሆኖም በዚሁ የኮታ ድልድል መሰረት እየተከናወነ አለመሆኑ፤ የሲሚንቶ የኮታ መነሻ በግልፅ የተቀመጠ ሁኔታ እንደሌለ እና ክልሎችና ከተማ አስተዳደር መሰረታዊ ሸቀጦች ምርቶቹ ካለመኖራቸው የተነሳ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እቅድ እና የአቅርቦት ጥያቄ ምላሽ የተሰጣቸው አለመሆኑ፣

52. የሲሚንቶ ምርት ኮታ በአምራቾች ፍላጎት እየተወሰነ መሆኑ፤ አከፋፋዮች ምርቱን በሚፈልጉት ወቅት ሳይሆን አምራቹ በሚፈልገው ጊዜ በአነስተኛ መጠንም እንዲወስዱ የሚያዟቸው መሆኑ እና አከፋፋዮች ሁሉም በሚባል ደረጃ አዲስ አበባ እየመጡ የሚሸጡ መሆኑ፤ አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች በህገ-ወጥ ከደላላ እየተረከቡ ያለደረሰኝ የሚሸጡ መሆኑ፣ በፋብሪካዎች አካባቢ ከፍተኛ የአቅርቦት ችግር መኖሩ እና የሲሚንቶ የሰርጭት ክፍተቶች መፍትሄ እያገኙ አለመሆኑ፤

53. ሚኒስቴር መ/ቤቱ መሰረታዊ ሸቀጦች በልዩ ሁኔታ ጊዜውንና በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቱን ለሕብረተሰቡ ማቅረብ የሚያስችላቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው ተቋማት ድጋፍ እንዲያገኙ እና ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ለማድረግ ከአስፈጻሚ አካላት ጠንካራ የቅንጅት ስራ አለመሰራቱ፤ በተለይ ድፍድፍ ዘይት ምርቱን ወደ ሃገር ውስጥ ለማስገባት የውጭ ምንዛሬ ከተፈቀደላቸው በኃላ አፈፃፀሙን ክትትል የማያደርግ መሆኑ፤

54.በተጨማሪም የሲሚንቶ በየስድስት ወሩ እና የድፍድፍ ዘይት በየሶስት ወሩ የፋብሪካ መሻጫ ዋጋ የሚተመን ሲሆን በተመኑ መሰረት ተግባራዊ አለመደረጉ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

<u>በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን በተመለከተ</u>፣

55. ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግሉ የጸደቀ እና ወቅታዊ የሆነ መመሪያ፣ ስታንዳርድ እና የዜጎች ቻርተር የሌለው መሆኑ፤

56.ተቋሙ ከድንበርና ከጎረቤት ሃገራት መሆናቸው አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ዜግነታቸው የሚጣራበት መመሪያ የሌለው መሆኑ፤ ዜግነት የማጣራት ስራው በልምድ የሚከናወን፣ ውሳኔው ዜግነትን በሚያጣራው ግለሰብ መልካም ፈቃድ ላይ የተመሰረተና ወጥ የሆነ አሰራር የማይከተል መሆኑ፤

57.ተቋሙ የአዲስ መደበኛ ፓስፖርት እና የፓስፖርት እድሳት አገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎቱን በምን ያህል ጊዜ እንደሚያገኙ የተቀመጠ መመሪያ እና የጊዜ ሰሌዳ የሌለው መሆኑ፤ ፓስፖርት በቀነ ቀጠሮ የማይሰጥ፤ በቀጠሮ ያልደረሰላቸው ተገልጋዮች ማንን መጠየቅ እንዳለባቸው የሚገለጽበት አሰራር አለመኖሩ እና አገልግሎቱን በወቅቱ ማግኘታቸውን የማይከታተል መሆኑ፤

58.የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 3 ላይ በህግ ካልተፈቀደ በስተቀር ማናቸውንም የመንግስት ገንዘብ መሰብሰብ እንደማይቻልና የመንግስት ገንዘብ እንዲቀበል ወይም እንዲሰበስብ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በአሁኑ ገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የተቀበለውን ወይም የተሰበሰበውን የመንግስት ገንዘብ ወደተጠቃለለው ፈንድ ገቢ እንደሚያደርግ፣ ገንዘብ የተቀበለበትን እና ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ መዝግቦ እንደሚይዝ ቢገልጽም፤

- ✓ ተቋሙ ገንዘብ ለመሰብሰብ መመሪያ የማውጣት ስልጣን ሳይኖረው በ21/12/2015 ዓ.ም የፓስፖርት ምዝገባ ቀን ቀጠሮ ያሳለፉ ግለሰቦችን በቅጣት ለማስተናገድ (የቅጣት ክፍያ ተመን) መመሪያ አዘጋጅቶ በዋና ዳይሬክተር ያጸደቀ መሆኑ፤

- ✓ የመንግስት የባንክ ሂሳብ የመክፈትና የመዝጋት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስልጣን ሆኖ ሳለ ተቋሙ የሂሳብ ቁጥር 1000569485782 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በግለሰቦች ስም ከፍቶ ገቢ የሚሰበስብ መሆኑ፤
- ✓ በአጠቃላይ አካውንቱ ከተከፈተበት እ.ኤ.አ ከ01/09/2023 እስከ 29/01/2024 ድረስ በአምስት ወራት ውስጥ **ብር 17,940,165.91 (አስራ ሰባት ሚሊየን ዘጠኝ መቶ አርባ ሺህ አንድ መቶ ስልሳ አምስት ብር ከ91/100)** ወደ አካውንቱ ገቢ የተደረገ ሲሆን፤

  ከዚህ ውስጥ የስራ ኃላፊዎቹ በቃል እንደለጹት ለትርፍ ሰዓት ክፍያ እና ለበዓል ለሰራተኛው ስጦታ **ብር 9,324,355.76 (ዘጠኝ ሚሊየን ሶስት መቶ ሀያ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሀምሳ አምስት ብር ከ76/100)** ለመንግስት ስራ የተሰበሰበን ገንዘብ ያለገንዘብ ሚኒስቴር ፈቃድ ወጪ የተደረገ መሆኑ እና እ.ኤ.አ በ29/01/2024 **ብር 8,615,810.15 (ስምንት ሚሊየን ስድስት መቶ አስራ አምስት ሺህ ስምንት መቶ አስር ብር ከ15/100)** በአካውንቱ ላይ ቀሪ የሚገኝ መሆኑን፤

59. ተቋሙ ቪዲቸር (Viditure) ከተባለ የግል ድርጅት ጋር እ.ኤ.አ ከመስከረም 6/2021 እስከ መስከረም 30/2024 የሚቆይ በ28/12/2013 ዓ.ም በገባው የውል ስምምነት መሰረት ከሀገር ውጭ ያሉ ነዋሪዎች ለፓስፖርት አገልግሎት ኦንላይን ሲያመለክቱ ሰነዱን አጣርቶ ወደ ኢሚግሬሽን የሚያስተላልፍ እና ፓስፖርቱ ተዘጋጅቶ ሲያልቅ ከኢሚግሬሽን ተቀብሎ ወደ ደንበኛው ተቋሙ ካወጣው የአገልግሎት ክፍያ በተጨማሪ **አንድ መቶ ዶላር** (100) በማስከፈል የሚያስተላልፍ ሲሆን ይህንን ስራ ለመስራት የተመረጠበትን መስፈርት፣ የግዥ ሂደት እና ፓስፖርትን ለማሰራጨት ፈቃድ (License) ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

    - ✓ ቪዲቸር ይህንን የፓስፖርት ስራ ለመስራት በሀገሪቱ የንግድ ህግ መሰረት ንግድ ፈቃድ ያላወጣ እና በታክስ ህጉ መሰረት ግብር የማይከፍል መሆኑ፤
    - ✓ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 እና በደንብ ቁጥር 449/2011 በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ላይ የፓስፖርት አገልግሎትን በውክልና እንደሚሰጥ የተገለጸ ነገር ሳይኖር አገልግሎቱን ቪዲቸር ለተባለው የግል ድርጅት የሰጠ መሆኑ፤

60. የሰራተኞች የስነ ምግባር መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን ጸድቆ ለሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመላክ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑንና የተቋሙ ሰራተኞች ተገልጋዩን በአክብሮትና በትህትና የማያስተናግዱ መሆኑ፤ ለማሳያ፡-

- ✓ የየተቋሙ ሰራተኞች ከበር ጥበቃ ጀምሮ አስተባባሪዎችና አገልግሎት የሚሰጡ ኦፊሰሮች ተገልጋዩን የማመናጨቅ፣ አልባሌ ቃላት የመጠቀም አልፎም የመነተት፣ የመገፍተርና የመማታት ሁኔታዎች መኖራቸውን በኦዲቱ ቡድኑ ባደረገዉ ምልከታ ያረጋገጠ መሆኑ፤

<u>የመንግስት የልማት ድርጅቶች የእዳ እና የትርፍ ድርሻ ክፍያ አፈጻጸም በተመለከተ፣</u>

61. አስተዳደሩ የእዳ እና የመንግስት የትርፍ ድርሻ ክፍያ ሥራዎችን ለማስፈጸም ቀደም ብለው በወጡት የህግ ማዕቀፎች (አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች) በልማት ድርጅቶች በተሟላ ሁኔታ በስራ ላይ በትክክል እየተገበረ እንዲሁም በአፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙትን ክፍተቶችን ለይቶ በማውጣት ከወቅቱ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ለማሻሻል የሚያስችል ውጤታማ የሆነ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ እንዲደረግባቸው በተሟላ መልኩ የተሰራ አለመሆኑ፣

62. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እዳ ወደ መንግስት ከመተላለፉ በፊት የተጠናው የጥናት ሰነድ በአስተዳደሩ እና በልማት ድርጅቶቹ የማይገኝ መሆኑ እንዲሁም ለኦዲት ቡድኑ የጥናት ሰነድ ተብሎ በገንዘብ ሚ/ር የቀረበው ሰነድ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እዳ ወደ መንግስት ከመተላለፉ በፊት የዕዳው ምንጭ፣ ሊከፈል ያልቻለበትን ምክንያትና በመንግስት ዕዳው ቢሸፈን ስለሚያስገኘው ጥቅም በማካተት የተሟላ ጥናት ስለመቅረቡ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ እና የልማት ድርጅቶች ያለባቸው እዳ በዝርዝር ያላስቀመጠ መሆኑ እንዲሁም እዳው ከተዛወረ በኃላ የመጣው ለውጥ ላይ የመገምገም ክፍተት ያለበት መሆኑ፤

63. በመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ስር ተጠሪ የሆኑ አምስት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እስከ ሰኔ 30/2015 ዓ.ም እንዲሁም የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን እስከ መስከረም 30/2023 እ.ኤ.አ በአጠቃላይ በብድር መክፈያ መርሃ ግብራቸው መሰረት ሳይከፍሉት የቀሩት **ብር 50,806,100,170.18 (ሃምሳ ቢሊዮን ስምንት መቶ ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ አንድ መቶ ሰባ ብር ከ18/100)** ያለ መሆኑ፤

64. አስተዳደሩ በ2015 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም መሰረት የልማት ድርጅቶች ያለባቸው ውዝፍ እዳና የትርፍ ድርሻ ቀሪ ክፍያ ብር 411,114,009.00 (**አራት መቶ አስራ አንድ ሚሊየን አንድ መቶ አስራ አራት ሺህ ዘጠኝ ብር**) ያለባቸው መሆኑ እንዲሁም የልማት ድርጅቶች በድምሩ ከ2013 እስከ 2015 ሳይሰበሰብ የቀረ **ብር** 12,109,739,569.71 (36.88%) ውዝፍ የትርፍ ድርሻ እዳ ያለባቸው መሆኑ፤

65. የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን በ2015 በጀት ዓመት የፋይናንስ ዕቅድ አፈጻጸም ማነስ ዋነኛ ምክንያት ከተለያየ የዉጭ አገር አበዳሪ አካላት **ብር** 1.8 **ቢሊዬን** ክፍያ መከፈል የሚገባው ያህል ብድር ባለመከፈሉ ዕዳው የተከማቸበት መሆኑና ከጠቅላላ ሀብቱ ዕዳዉ ወደ 126% ኦዲቱ እስተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ከፍ ያለ መሆኑ እና በፋይናንስ አቅሙ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድርዋል፡፡

66. በመሆኑም አስተዳደሩ የልማት ድርጅቶች የዕዳና የትርፍ ድርሻ ክፍያን ስራዎችን ለማስፈፀም ቀደም ብሎ የወጡና የህግ ማዕቀፎች (አዋጅ፣ ፖሊሲ፣ ደንብ፣ መመሪያ)፣ ስትራቴጂ በስራ ላይ ወጥ በሆነ መልኩ በትክክል መተግበሩን፣ እንዲሁም የልማት ድርጅቶች በተሰራጨላቸው መመሪያዎች መሠረት የራሳቸውን አስራር ስርዓት የሚሰሩ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ የህግ ማዕቀፎች የአፈጻጸም ክፍተቶችን ለይቶ እንዲታረሙ፣ የልማት ድርጅቶችን አመራር አቅምንና አሰራር እንዲሻሻል እና ለውጥ እንዲመጣ በህጉ መሠረት የማይፈጽሙ አካላትን ተጠያቂነትን እንዲረጋገጥና በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃ እንዲደረግባቸው የሚያስችል ችግር ፈቺ ሥራ ሊሰራ እንደሚገባ በላክነዉ ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የከተሞች የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ እና የሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ግንባታ አፈጻጸም በተመለከተ፡</u>

67. የሳኒቴሽን መሰረተ ልማት የሚመራበት ፖሊስ ፣የሳኒቴሽን የጥናትና ዲዛይን፣ የግንባታና የተቋማት አስተዳደር እና የሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ከተገነባ በኋላ የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝ አወጋገድ ሥርዓት ዙሪያ/ያሉት ችግሮች ላይ ክትትል ለማድረግ የሚያስችል ማኑዋል በማዘጋጀት በክልሎች ተግባራዊ እንዲያደርጉት ያልተላከ መሆኑ፤

68.የሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ለአብነት (የደቡብ አቃቂ ፍሳሽ ተፋሰስ በቀን 60ሺ.ህ ሜትር ኩዩብ ፍሳሽ ማጣራት ለሚችል ፕሮጀክት ጥናቱን አጠናቆ መስከረም/2016 ያቀረበ ቢሆንም፤ጥናቱን ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር አቅርቦ እንዲገመገም ያልተደረገ መሆኑ፤

69.ሚ/ር መ/ቤቱ የከተሞች ሳኒቴሽን መሠረተ ልማት ግንባታ ሥራዎች በውሉ መሠረት የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው በተያዘላቸው ጊዜና በጀት መከናወናቸውን ለማረጋገጥ ወቅታዊ ወይም ተከታታይ የሆነ ክትትልና ግምገማ በማድረግ ግብረ-መልስ የሚልክበት ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ሲኖርበት፡

- የ3 ከተሞችን (ጋምቤላ፣ አሶሳ፣ ሰመራ ሎጊያ) ጥናትና ዲዛይን ስራ ለማሰራት በአንድ አመት(በ300 የስራ ቀን) ውስጥ አጠናቆ ለማቅረብ በታህሳስ 2012 በጀት ዓመት ውል ተገብቶ ጥናቱ በጥር/2015 ዓ.ም የተጠናቀቀ ሲሆን፤ ጥናቱ በውሉ ላይ ከተጠቀሰው ጊዜ በላይ ሦስት አመት የዘገየ መሆኑ፣
- የምስራቅ ተፋሰስ ፍሳሽ ፕሮጀክት (በቀን 104 ሺ.ህ ሜትር ኪዩብ ፍሳሽ ማጣራት የሚችለው ፕሮጀክት) የአዋጭነት ጥናት፣ በሰኔ 2015 ዓ.ም አማካሪ መሃንዲሱ አጠናቆ ያቀረበ ሲሆን፤ ጥናቱን ማቅረብ ከሚገባው ከተዋዋሉበት ጊዜ (አንድ ዓመት ከስምንት ወር ዘግይቶ የተጠናቀቀ መሆኑ፣
- በ2015 በኦሮሚያ ክልል ስር ለሚገኙ ሶስት ከተሞች (አሰላ፤ ቢሾፍቱ እና ሻሸመኔ) የግንባታ ኮንትራክተር ቅጥር በማከናወን ስራውን ወደ 28% ለማድረስ ሙያዊ እገዛ መስጠት፡- እስከ አራተኛው ሩብ ዓመት 28% ለማከናወን ታቅዶ ሥራው ያልተከናወነ መሆኑ፤
- በኦሮሚያ ክልል ስር ለሚገኙ ሁለት ከተሞች (ጅማ እና ነቀምቴ) የግንባታ ኮንትራክተር ቅጥር በማከናወንና ሙያዊ እገዛ በመስጠት እስከ 2015 አራተኛዉ ሩብ ዓመት 28% ለማከናወን ታቅዶ፤ ሥራዉ ያልተከናወነ መሆኑ፤

70.በ2015 በጀት ዓመት በ8 ከተሞች 67 የህዝብና 95 የጋራ መፀዳጃ ቤቶች በአጠቃላይ 162 መጸዳጃ ቤቶችን የእድሳት ስራ ለማከናወን ታቅዶ የነበረ ቢሆንም፤ አፈጻጸሙ ግን በቁጥር 25 የመፀዳጃ ቤቶች ወይም 15% ብቻ ስለታደሱ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፤

71.ደብረብርሃን ከተማ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ከከተማው በ13 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ አጠገብ በአጥር ታጥሮ ያለ ቢሆንም፤ የአካባቢው ህብረተሰብ እንስሳት ሞተዉባቸው ባቀረቡት ቅሬታ አሁን አገልግሎት እየሰጠ እንዳልሆነና ከየመኖሪያ ቤቱና ሌሎች ድርጅቶች የሚፈሰው ፍሳሽ ቆሻሻ በቀጥታ ወደ ወንዝና በገበሬዉ ማሳ እየተደፋ ሲሆን፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፍሳሽ ማስወገጃ ግንባታውን ለመገንባት እስከሁንም በጥናት ደረጃ ያለ መሆኑ፤

72. በጅግጅጋ ከተማ ባደረገው የከተማው ስታንዳርዱን የጠበቀ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ እንደሌለውና በከተማው በርቀት ላይ በተቆፈረ ጉድጓድ (land fill) ላይ ፍሳሹ የሚወገድ ሲሆን፤ ጉድጓዱ ሞልቶ ወደ አካባቢው ማህበረሰብና ወደ ወንዞች በመፍሰስ ወንዙም ወደ አራርሶ ከተማ፣ ደገ ሃቡር፣ ጎዴ ከተሞች ጋር በመድረስ የአካባቢው ማህበረሰብ እንደሚጠቀሙት እና እንስሳት እንደሚጠጡት፤ እንዲሁም ወደ ሸበሌ ወንዝ በመቀላቀል የአካባቢው ማህበረሰብ ለመጠጥ አገልግሎት እያዋለው ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአፋጣኝ ወደ ግንባታ ገብቶ ችግሩን ለመቅረፍ የዘገየ መሆኑ፤

73.በአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የአቃቂ ተፋሰስ፣ በቃሊቲ ተፋሰስ፣ በምስራቅ ተፋሰስ፣ በሦስት አመታት (ከ2013-2015 ዓ.ም) ከተጠናው ከ623.69 ኪ.ሜ የመስመር ዝርጋታ ጥናትና ዲዛይን ውስጥ ወደ ተግባር ወይም የፍሳሽ መስመር ዝርጋት የተከናወነው 392.31 ኪ.ሜ ወይም 63 ፐርሰንት ብቻ ሲሆን ቀሪው 231.38 ኪ.ሜ ወይም 37 ፐርሰንት ለጥናቱ ወጪ የወጣበት ቢሆንም፤ የፍሳሽ መስመር ዝርጋታ ጥናትና ዲዛይን ወደ መስመር ዝርጋታ ያልተቀየረ መሆኑ ታውቋል፣

በጤና ሚኒስቴር የፌዴራል ሆስፒታሎች ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ፣

74.የፌዴራል ሆስፒታሎች (በሀዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል፣ በዲላ አጠቃላይ ሆስፒታል፣ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊንየም የሕክምና ኮሌጅ፣ በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል) የሚመነጨውን ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በተመለከተ ከፍተኛ ክፍተቶች እና ችግሮች ቢኖሩም በየአመቱ ችግሮቹን በሪፖርት ከመግለጽ በዘለለ ክፍተቶችን መሰረት ያደረገ ጥናት የሌለ መሆኑ፣

75.በፌዴራል ሆስፒታሎች የሚሰጡትን አገልግሎት በአዋጅ 299/1995 አንቀጽ 5 መስረት የአካባቢን እና ማህበረሰብን ሊጎዱ የሚችሉ አደገኛ ቆሻሻ ከሚያመነጩ ተቋማት የሚመደብ በመሆናቸው ፕሮጄክቶች/ ሆስፒታሎቹ ከመሰራታቸው በፊት የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት (Environmental Impact Assessment) እንዲያዘጋጁ

ወይም ከአዋጁ ቀድሞ ያለ ጥናት የተቋቋሙ ከሆነ ደግሞ የአካባቢ አስተዳደር እቅድ ማዘጋጀት (environment management plan) እንዳለባቸው ቢገልጽም ከአዋጁ በኋላ የተሰሩ የኤካ ኮተቤ ሆስፒታል፣ እንዲሁም አዳዲስ የማስፋፋያ ስራ ፕሮጀክት የሰሩ ሆስፒታሎች መካከል ዲላ ሆስፒታል፣ ሀዋሳ ሪፈራል ኮምፕሬሲቭ ሆስፒታል፣ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ፣ ሕይወት ፋና ኮምፕሪንሲቭ ሆስፒታል እና አለርት ስፔሻላይዝድ ሆሰፒታል የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ጥናት ወይም የአካባቢ አስተዳደር እቅድ ያላዘጋጁ መሆናቸው፤

76.በዲላ አጠቃላይ ሆስፒታል ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችና ኬሚካሎች በስቶር ውስጥ የተቀመጠ ቢሆንም፤ ሆስፒታሉ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ የተበላሹ እና የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈ መድኃኒቶች የከተማው ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ በተዘጋጀ ስፍራ ከመመሪያ ውጭ በሆነና የሚያስከትለው ጉዳት ባልተጠና መልኩ በመቅበር ያስወገዱ መሆኑ፣

77.ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች ከዚህ በፊት አዳማ ማቃጠያ ቦታ የሚቃጠል ቢሆንም፤ አሁን ማስወገጃ ቦታ ባለማግኘት ሳይወገድ ለረጅም ጊዜ የተቀመጠ መሆኑ፣

78.በጅግጅጋ ሃስን የበሬ ሆስፒታል የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችን ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጣ ኮሚቴ ተዋቅሮ በ2005 ዓ.ም የወጣውን ከሕክምና አገልግሎት የሚወጡ የቆሻሻ አስተዳደር መመሪያ (Health care waste management) መሰረት ሳይሆን ከከተማ ውጭ በሜዳ ላይ የሚቃጠሉ መሆኑ፣

79.በአለርት ሆስፒታል የአገልግሎት ጊዜአቸው ያለፈ መድኃኒቶች የሚወገድበት ቦታ ባለመኖሩ ስቶር ውስጥ ከ3 አመት በላይ ሳይወገድ የተቀመጠ መሆኑ፤

80.በጴጥሮስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች በብዛት የተከማቸ መሆኑ እና በተገቢው መንገድ ያልተቀመጠ መሆኑ፤ ከቆርቆሮ እና ከተሰባበረ ጣውላ በተሰራ እና ለዝናብ በተጋለጠ መልኩ የተቀመጠ መሆኑ፣

81.በሃዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል አካባቢ ያሉ ነዋሪዎችና በሃይቁ ላይ የአሳ ማስገር ስራ ላይ የተሰማሩ ማህበራት ከሆስፒታሉ የሚወጣው ፍሳሽ የተበከለና በሃይቁ ውስጥ ላሉ ብዝሀ-ህይወት አሳሳቢ መሆኑን ቢናገሩም ቅሬታው ያልተሰማ መሆኑ እና ከህብረተሰቡ የሚነሳው ቅሬታ የሚያስተናግድበት የስልክ መስመር የማይሰራ በመሆኑ ቅሬታ ለማቅርብ የተቸገሩ መሆናቸዉ በኦዲቱ መታየቱ፣

82.በአለርት አጠቃላይ ሆስፒታል የአመድም ሆነ የእንግዴ ልጅ(የፕላሴንታ) መቅበሪያ ቦታ ባለመኖሩ ምክንያት ፕላሴንታ በግቢ ውስጥ በሚገኘው ዛፎች ውስጥ ዝቅተኛ ቦታ ላይ ለእንስሳትና ለዝናብ ክፍት በሆነ መልኩ ተከማችቶ መኖሩና ከማቃጠያ የወጣውም አመድ በ5 የተለያዩ ቦታዎች የተከማቸ መሆኑ፣

83.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሆስፒታሎች የሚመነጭ የኬሚካል ፍሳሽ ቆሻሻ የህብረተሰቡን ጤና እና አካባቢን በማይጎዳ መልኩ ስለመወገዳችው እና በአግባቡ ስለመታከማቸው የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያና ማከሚያ (Waste Water Treatment plant) መኖሩን ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል በተጨማሪም ከፌደራል ሆስፒታሎች የሚመነጨውን ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በተገቢው መንገድ ተይዞ መወገድ እንዲችል ሚ/ር መ/ቤቱ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እንዳለበት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>በኢትዮጵያ ሎተሪ አገልግሎት በፍቃድ ለሚሰሩ ለሌሎች አካላት የዕድል ሎተሪ እንዲያጫውቱ የሚደረግበት የፍቃድ አሰጣጥ እና ገቢ አሰባሰብ በተመለከተ፣</u>

84.በአዋጅ ቁጥር 160/2001 አንቀጽ 6(4) በፍቃድ የዕድል ሎተሪ ጨዋታን ለሚያጫውቱ አካላት ፍቃድ የመስጠት እና የመቆጣጠር ስልጣንና ተግባር ለአገልግሎቱ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 27 ቀ፣ በ፣ ተ መሰረት ለገቢዎች ሚኒስቴር የተሰጠው ቢሆንም አገልግሎቱ ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋር በመሆን በአዋጁ የተሰጣቸውን አሁናዊ ኃላፊነት ለማስተግበር የየተቋማቸውን አደረጃጀትና ስልጣንና ተግባር የሚደነግግ ረቂቅ ህግ እንዲወጣ እና በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ በማቅረብ ለገቢዎች ሚኒስቴር ስራውን ያላስረከበ መሆኑ፤

85.በናሙና በታዩ የስፖርት ውርርድ ተጫዋቾች እድሜያቸው ከ19-30 የሚሆኑ ወጣቶች 57.5% ዕድሜያቸው 31-40 የሆኑት 28.9% እድሜያቸው ከ41-50 የሚሆኑ 1.3% መሆናቸውን የሚገልጽ ሲሆን ይህም አብዛኛው በተማሪና ሰራተኛ እድሜ ክልል የሚገኙ ግለሰቦች በብዛት የሚጫወቱ መሆኑን በኦዲቱ ታይቷል፤

86.ስፖርት ውርርድ እንደ ሱስና ቁማር በሚሆንበት ጊዜ የተለያዩ የህብረተሰብ ጤና ስጋት ተደርጎ የሚወሰድ እንዲሁም የስነልቦና ጫናዎችን፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎችን የሚያስከትል መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ጥናቶች ያረጋገጠ መሆኑ፡

87.ከአገልግሎቱ ፍቃድ በማውጣት የዕድል ሎተሪ ጨዋታን የሚያጫውቱ አካላት በገቡት ውል መሰረት ስራቸውን እየሰሩ ስለመሆናቸው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤

88.አገልግሎቱ በፍቃድ የሚሰሩ የዕድል ሎተሪ ጨዋታዎች እና ህገ ወጥ የዕድል ጨዋታዎችን በተመለከተ በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች (በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጣ በመሳሰሉት) በአመታዊ ዕቅድ በመያዝ ለማህበረሰቡ የግንዛቤ የማስፋፋት ስራ ያልተሰራ መሆኑ፣

89.አገልግሎቱ በፍቃድ ስለሚሰሩ የዕድል ሎተሪ ጨዋታዎች እና ህገ ወጥ የዕድል ጨዋታዎችን ሊቆጣጠር እንዲሁም የሚያስከትሉትን ተፅዕኖ በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች (በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጣ በመሳሰሉት) ለማስገንዘብ በአመታዊ ዕቅድ በመያዝ ለህብረተሰቡ የግንዛቤ የማስፋፋት ስራ ሊሰራ እንደሚገባ በላክነዉ ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>**በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትና የአየር ጠባይ የማላመድ እና ስርየት አፈፃፀምን በተመለከተ፣**</u>

90.ኢንስቲትዩቱ ለከፍታ አየር ሁኔታ መከታተያ የሚጠቅሙ 800 እና 30 ግራም ባሎኖችን ሃይድሮጂን አዘጋጅቶ በመሙላት በፓይለት ባሎንና በሬድዮ ሶንዴ በቀን ሁለት ጊዜ መረጃ ለመሰብሰብ በ2014 ዓ.ም በ12 ወራት 578 ለማከናወን በዕቅድ ይዞ የነበረ ቢሆንም 89 ወይም 15 ፐርሰንት ብቻ ያከናወነ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት ደግሞ ምንም አይነት ዕቅድ ያልተያዘና ያልተከናወነ መሆኑ፣

91.የጤናውን ዘርፍ ለማገዝ የሚያስችሉ ከአየር ጠባይ ጋር ቁርኝት ላላቸው በሽታዎች (አስም፣ ሳምባ በሽታ፣ ፖሊዮ፣ ፈንጣጣ፣ ኮሌራ የመሳሰሉት) በጊዜና በቦታ መቆጣጠር የሚያስችል የጤና ሚቲዎሮሎጂ ገደቦችን ለማዘጋጀት በ2015 በጀት ዓመት በዕቅድ የተያዘው ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣

92.ኢንስቲትዩቱ ካቋቋማቸው እና ከሚያስተዳድራቸው 1303 (210 አንደኛና ሳይኖፕቲክ እንዲሁም 1093 3ኛና 4ኛ ደረጃ) የተለያዩ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል 124 የሚሆኑ (1ኛ ደረጃ፣ አውቶማቲክ፣ 3ኛ ደረጃ እና 4ኛ ደረጃ) ጣቢያዎች አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፣

93.ኢንስቲትዩቱ ስለሰብሎች የዕድገት ሁኔታ የሚገልፅ መረጃ እንዲሰበሰብ የሚጠበቅበት ቢሆንም፤ እንዲህ አይነቱን መረጃ ለመሰብሰብ ምቹ ሁኔታ ያላቸው ጣቢያዎች ይህንን የጣቢያውን ይዞታ መሬት የሰብል የዕድገት ሁኔታ ክትትል ለማድረግ እየተጠቀሙበት እንዳልሆነ፣ እንዲሁም ለግብርናው ምክር የሚያገለግሉ የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች በበርካታ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች የሌሉ፤ እና ያሉትም የማይሰሩ መሆኑ፣

94. በሁሉም ጥበቃ በሚያስፈልጋቸው 1ኛ ደረጃ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግላቸው የሚገባ ቢሆንም፤ በተለይ 1ኛ ደረጃ ጣቢያዎች ሰፊ ይዞታና በርካታ የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች ቢኖራቸውም ከመረጃ ሰብሳቢ ባለሙያ (ኦብዘርቨር) በስተቀር ጥበቃ የሌላቸው በመሆኑ መሳሪያዎቹ እና የአጥር ብረቶች ለስርቆት እየተዳረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዚህም ኢንስቲትዩቱ የተቋቋመበት ዓላማን ባግባቡ ለመተግበር የሚያስችሉ ማሻሻያ ሃሳቦች በኦዲቱ ተሰጥተዋል፡፡

<u>በኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የፓወር ኢኪዩፕመንት ማምረቻ ኢንዱስትሪ የማምረቻ ፋብሪካዎች የሥራ አፈፃፀም እና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓትን በተመለከተ፡</u>

95. ኢንዱስትሪው የማምረቻ ማሽን የምርት አቅም እና የሰው ኃይልን መሠረት በማድረግ ቀድሞ ገበያ በማፈላለግ የደንበኛ ትዕዛዝ ተቀብሎ ውል በመግባት ምርት አለማምረቱ እንዲሁም ኢንዱስትሪው ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር የገባውን የምርቶች አቅርቦት በገባው ውል መሰረት በወቅቱ ያልተፈፀሙ መሆኑ፣

96. ኢንዱስትሪው ለሰንዳፋ ሶላር ፓኔል ማምረቻ ፋብሪካ በብር 47,818,657.03 በ2007ዓ/ም የተገዛው የሶላር ፓኔል ማምረቻ ማሽን የግዥ ሂደት የተመራበት መንገድ የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

97. በኢንዱስትሪው ስር በሚገኙ ፋብሪካዎች ሊወገዱ የሚችሉ የተለያዩ ንብረቶች ቢኖሩም በሚመለከተው አካል ተጠንቶ የሚወገዱ ንብረቶች ያልተለዩና የዋጋ ግምት ያልወጣላቸው መሆኑ፣ ለአብነት በሞጆ ዋየርና ኬብል ማምረቻ ፋብሪካ 74,725 ቶን የገንዘብ መጠኑ ብር 7,646,106,350.75 የሆነ የኬብል ፕላስቲክ መስሪያ ኬሚካል ግብዓት (MV cable material polyetien compound KL-XL-09) የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈበት ኬሚካል ሳይወገድ በመጋዘን ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፣

98. ፋብሪካዎች ለሚያመርቷቸው ምርቶች ደረጃ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት (እስታንዳርድ) ያልተቀመጠላቸው፤የምርት ሰርተፊኬሽን ያላገኘ እና አለምቀፍ ደረጃን መሰረት ያላደረገ እንዲሁም ኢንዱስትሪው በትራንስፎርመር ምርት ዝቅተኛ መለኪያ ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት የምርት ሰርተፊኬሽን ያላገኘ መሆኑ ታውቋል።

<u>በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት መኖ አቅርቦትና ስርጭት አፈፃፀም በተመለከተ፣</u>

99. የእንስሳት መኖ ምርታማነትን ለመጨመር የሚያስችሉ አዳዲስ የመኖ የመነሻ/የመኖ ዘሮች የሚሰራጩበት እና ግብይት የሚደረግበት ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት የሌለ መሆኑ እና የመነሻ ዘር በመውሰድ መኖን የሚያባዙ ድርጅቶች የማይታወቁ በመሆኑ፤ ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ ያልተቻለ መሆኑ፤

100. የእንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃዎች አምራች አስመጪ ጅምላ አከፋፋይ፣ላኪ እና ችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች የምዝገባና የስራ ፈቃድ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርትን ለመወሰን የወጣው መመሪያ 02/2010 ክፍል 2 ተራ ቁጥር 2 የመኖ ያለቀለት ምርት መደርደርያ ጣውላ ወይም ፕላስቲክ ፓሌት ላይ መቀመጥ እንዳለበት የሚገልፅ ቢሆንም፤ በናሙና ካየናቸው ሁለት የመኖ ማቀነባበሪያ ያመረቱት ምርት ለአፍላ ቶክሲን (ሻጋታ) በሚያጋልጥ መልኩ መሬት ላይ ተቀምጦ መገኘቱ፤

101. የዕፅዋት ዘር ግብዓት ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 464/2013 ክፍል 1 ገፅ-3) እና አዋጅ ቁጥር 782/2005 አንቀፅ 20 ንኡስ አንቀፅ 1 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከአንድ ክልል በላይ የዕፅዋት ዘር(የእንስሳት መኖ ዘር) በማከፋፈል ለሚሰማሩ አምራች ወይም አከፋፋይ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሊሰጥና ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባ የሚገልፅ ቢሆንም፤ በናሙና ተመርጠው ከታዩ ባለድርሻ አካላት ለማወቅ እንደተቻለው በአንድ ክልል ላይ የመኖ ዘር የሚያመርቱ ድርጅቶች በተለያዩ አካላት የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጣቸው መሆኑ፤ ይህም በክልሉ ግብርና ቢሮ፣ በግብርና ሚኒስቴር እና በግብርና ባለስልጣን የሚሰጥ መሆኑ፤ በተጨማሪም ክልሉ ክትትል በሚያደርግበት ወቅት የብቃት ማረጋገጫ ሳይሰጣቸው ከኢንቨስትመንት ቢሮ ፈቃድ በማግኘት የመኖ ዘር ማምረት ስራ ላይ የተሰማሩ የመኖ ዘር አምራቾች መኖራቸውን፤ ይህም ተቀናጅቶ የመስራት ችግር መኖሩን እና በመኖ ዘር ማምረት ስራ ላይ የሚሰጡ ፈቃዶች ወጥነት የሌላቸውና ለመከታተል አመቺ አለመሆናቸው፣

102. የመኖ ደረጃዎች በደረጃዎች ኢንስቲትዩት የፀደቁ 45 የመኖ ደረጃዎች መኖራቸው ነገር ግን በናሙና የታዩ የመኖ አቀነባባሪዎች የመኖ ደረጃዎችን እንደማያውቋቸው እና ያልደረሷቸው እና በደረጃዎች ኢንስቲትዩት የተዘጋጀውን የመኖ ደረጃዎች ለሚመለከታቸው አካላት ወደ ታች በማውረድ እንዲተዋወቁ እና እንዲተገበሩ ያልተደረገ መሆኑ፤

103. በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት የመኖ ኢንቨስትመንትና ምርት ግብይት የተመለከቱ የሀገር ውስጥና የውጭ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ሊያስፋፋ እንዲሁም አምራቾች በሀገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ንግድ ትርዒቶች እንዲሳተፉ የተመቻቹ ሁኔታዎች አለመኖራቸዉ ታዉቋል።

<u>በኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት የወራሪ መጤ ዝርያዎችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ለማጥፋት የተዘረጋ ሥርዓትን በተመለከተ</u>፡

104. ኢንስቲትዩት ወራሪ መጤ ዝርያዎች ከመከሰታቸው በፊት የቅድመ መከላከል ስራዎች በየደረጃው የሚተገበሩበትን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ቢኖርበትም ወራሪ መጤ ዝርያዎች በሀገሪቱ ከመከሰታቸው በፊት የቅድመ መከላከል ስራዎች በየደረጃቸው የሚተገበሩበት የአሰራር ስርአት መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ያልተደረገ እና ወራሪ መጤ ዝርያዎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በየኬላዎቹ የሚወጡትንና የሚገቡትን ብዝሀ-ህይወት የሚቆጣጠር ባለሙያ የሌለ መሆኑ፤

105. ኢንስቲትዩቱ ብሄራዊ ፓርኮች፣ትላልቅ ወንዞች፣ ሀይቆች፣ የውሃ ግድቦች እና ደኖች እና በውስጡ የሚገኙ ብዝሀ ህይወቶች በወራሪ መጤ ዝርያዎች እንዳይጠቁ የሚጠበቁበት የአሰራር ስርአት የሌለው መሆኑ፤

106. ኢንስቲትዩቱ በወራሪ መጤ ዝርያዎች የተወረሩ አካባቢን በመለየት አካባቢን በማይጎዳ መልኩ በማጽዳት የጸዳውን መሬት መልሶ የማልማት ተግባር ያልተከናወነ መሆኑ፣

107. ኢንስቲትዩቱ ወራሪ መጤ ዝርያዎችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ለማጥፋት የተቀናጀ እና የተደራጀ ብሄራዊ መረጃ ክምችት(ዳታ ቤዝ) አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያላደረገ፣ ወራሪ መጤ ዝርያዎችን በተመለከተ በሀገሪቱ ባሉ ክልሎች ወራሪነታቸው የተረጋገጡ አረሞችን የሚለይበት መረጃ የሌለ እና በሀገሪቱ በሚመለከታቸው ተቋማት ወራሪ መጤ ዝርያን በተመለከተ ወቅታዊ የሆነ መረጃ የሚገኝበት ዳታ ቤዝ የሌለ መሆኑ፤

108. ወራሪ መጤ ዝርያዎችን በሀገሪቱ ትኩረት ተሰጥቶበት በጀት፣ፖሊሲና ስትራቴጂ ተነድፎለት በሁሉም ክልሎች ዞኖችና ወረዳዎች በመንግስት ባለው መዋቅር ውስጥ በባለቤትነት መምራት የሚችል አካል የሌለ መሆኑ እና ወራሪ መጤ ዝርያን በተመለከተ በተለያዩ አካላት የተደረጉ የጥናት ውጤቶች ወደ ባለድርሻ አካላት ወርደው ተግባራዊ ያልተደረጉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፤

109. ኢኒስቲቲዩቱ የወራሬ መጤ ዝርያን የሚያጠፋበትን መንገድ ከሚመለከታቸዉ አካለት ጋር ስልት ነድፎ መንቀሳቀስ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል

<u>በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የምግብ ሳይንስና ስነ-ምግብ ምርምር ፈንድ አጠቃቀምን በተመለከተ፣</u>

110. በኢንስቲትዩቱ ማኔጅመንት አመራር መጋቢት 2011 ዓ.ም በወጣ የoverhead መመሪያ ነገር ግን በሚመለከተው አካል ባልጸደቀ ከእያንዳንዱ ለምርምር ስራ ከሚመደበው ፈንድ ላይ 15% አስተዳደራዊ ወጪ (overhead cost) ተብሎ እየተቆረጠ በኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊ ፈቃድ ከፕሮጀክቱ አላማ ዉጭ ለተለየዩ አገልግሎቶች የሚዉል ሲሆን በዚሁ መሰረትም ከ2011ዓ/ም-2015 ዓ/ም /overhead cost/ ወጪ ተብሎ ከተቆረጠው ብር 59,591,189. ውሰጥ ብር 33,014,425 ለኢንስቲትዩቱ ለተለያዩ አገልግሎቶች የዋለ መሆኑ፤

111. ኢንስቲትዩቱ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የጥቅማ ጥቅም ተመን ሳይኖር ባወጣው የጥቅማ ጥቅም መመሪያ መሠረት ለምርምር ሥራ ከመጡ ፕሮጀክቶች /ፈንዶች/ ላይ ለኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች እና ኃላፊዎች የማበረታቻ ክፍያ ከ2012 ዓ/ም-2015ዓ.ም ብር 27,169,453.91/ ሃያ ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ ስልሳ ዘጠኝ ሺ አራት መቶ ሃምሳ ሶስት ከዘጠና አንድ ሣንቲም/ የተከፈለ መሆኑ፤

ለምርምር የሚመደበውን ገንዘብ /ሀብት/ ለምርምር ተግባር ብቻ ማዋሉን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ እና ኢንስቲትዩት የሚያከናውናቸው ምርምሮችን በተያዘላቸው ጊዜ የማይጠናቀቁ ፕሮጀክቶች መኖራቸው፣

112. በኢንስቲትዩቱ ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ በገንዘብ ሲተመን ብር 70,799,745.16 /ሰባ ሚሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺ ሰባት መቶ አርባ አምስት ከ16 ሳንቲም የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው እና ያልተወገዱ ለምግብ ምርምር እና ለሌሎች የኢንስቲትዩቱ ሥራዎች የተገዙ ኬሚካሎች እና የላቦራቶሪ ሪኤጀንቶች ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ለ45 ዓመታት ተከማችተው ሳይወገዱ በመጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡

113. በሁሉም የክዋኔ ኦዲት እና አካባቢ ኦዲቶች ላይ የተገኙትን ግኝቶች መሰረት በማድረግ ተቋማቱ በኦዲቱ የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦችን መነሻ አድርገው የድርጊት መርሃ ግብረ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ እንዲገቡ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የተከበሩ አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ የመንግስት ወጪ አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋ/ ኮሚቴ ሰብሳቢ!

የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

<u>የመ/ቤታችን ዋና ዋና የድጋፍ ዘርፍ አፈጻጸምን የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን በተመለከተ፣</u>

114. የመ/ቤታችን የአስር አመት መሪ እቅድን መነሻ ተደርጎ ከተዘጋጀዉ አስትራቴጂክ እቅድ የአመቱን እቅድ በዉጤት ተኮር ሥርዓት ግንባታ ተከትሎ ለእያንዳንዱ ሰራተኛ ስራን ቆጥሮ በመስጠት ሥራዎቹ እስከ ሠራተኛ ድረስ እንዲወርድ ተደርጓል፡

115. የተቋሙን ስትራቴጂክ እቅድ በመከለስ እና የትኩረት አቅጣጫዎች የአፈፃፀም አመልካቾችን (Performance Indicators) እንዲሁም የኦዲት ሥራ ውጤት (Audit Effectiveness) በአዲስ መልክ የተቀረጸ ሲሆን አፈጻጸሙም ወቅቱን ጠብቆ እንዲሞላ ተደርጓል፡፡

116. ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ከሀምሌ 2015 እስከ መጋቢት/2016 በ9 ወራት ውስጥ የተለያዩ አገልግሎት ለማግኘት ወደ መ/ቤታችን የመጡ ወንድ 290 ሴት 121 በድምሩ 411 ተገልጋዮች በአግባቡ ከመ/ቤቱ የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

117. ቀድሞ የነበረውን የተቋሙን የዜጎች ቻርተር ወቅታዊ ከማድረግ አንጻር እንዲከለስ ተደርጓል፡፡

118. የስነምግባር ጉድለት የታየባቸው 2 ሰራተኞች ተገቢውን ቅጣት በመቅጣት ለሌሎች ሰራተኞች ትምህርት እንዲሆን ተደርጓል፡፡ የተቋሙ የሥጋት ተጋላጭነት ደሰሳ ተከናውኗል። የተሻለ አፈጻጸም ያሰዩ ሰራተኞችም የእዉቅና ሽልማት ተሰጥቷል ።

119. በአለም አቀፍ የኦዲት ስታንዳርድ መሰረት የኦዲት ሥራአስኪያጆች እንደአስፈላጊነቱ የስራ ስብጥር ወይም ሪሻፍሊንግ የተከናወነ ሲሆን በመስክ የሚደረገው የክትትል (supervision) ሥራ በተከታታይነት ተከናውኗል፡፡

120. በተቋሙ ረዘም ያለ እድሜ ያስቆጠሩ እና ወቅታዊ መሆን ያለባቸዉ ስድስት መመሪያዎችን ማሻሻያ የተቻለ ሲሆን አንድ አዲስ መመሪያ የመስሪያቤቱ ደንብ በሚፈቅደዉ በማዘጋጀት እና በማጸደቅ መተግበር ትችሏል፡፡

ሴክተር ዘለል ሥራዎችን በተመለከተ፣

121. በፋይናንስ እና ህጋዊነት እንዲሁም በክዋኔ ኦዲቶች ለሴቶች፣ ወጣቶች፣ ለአካል ጉዳተኞችና ለአረጋውያን በህግ የተጠበቁ መብቶች ተጠቃሚነትና የአገልግሎት ተደራሽነት በተመለከተ ሁሉም የሥራ ክፍሎች የሥርዓተ ፆታ ጉዳይን የዕቅዳቸው አካል አድርገው እንዲያቅዱና በኦዲቱ ትኩረት ሰጥተዉ እንዲያዩት ተደርጓል፡፡

122. ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የመ/ቤታችንን ሴት ሠራተኞች ተጠቃሚ ለማድረግ በተደረገው ጥረት በግማሽ ክፍያ በማስተርስ፣ በዲግሪ፣ ሙያ እና ቴክኒክ ደረጃዎች 54 ሴቶች የትምርት ዕድል ያገኙ ሲሆን ለ40 ሴት ሠራተኞች የንግድ ክህሎት፣ የስራ ፈጠራና ስርዓተ-ፆታ በሚሉ ርዕሶች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

123. በመ/ቤቱ የህፃናት ልጆች ማቆያ አገልግሎት በማዘጋጀት እና 2 ተንከባካቢ ነርሶችን በመቅጠር 12 ሕፃናት (7 ወንድና 5 ሴት) የቀን እንክብካቤ ማቆያ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

124. የገና በዓልን ምክንያት በማድረግ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ነዋሪ ለሆኑ 30 አካል ጉዳተኞችና 80 አረጋዊያን የአልባሳት ስጦታ ተበርክቷል፡፡

125. የ2016 ዓ.ም አዲስ ዓመት በዓልን ምክንያት በማድረግ 75 ለሚሆኑ የመ/ቤቱ ሠራተኞች ከሰራተኛው የመዝናኛ ክበብ በተገኘ ገቢ የብር 187,500 ድጋፍ ተደርጓል፡

126. ሴቶችን አመራርነት ደረጃ ከማምጣትና ከማብቃት አንጻር በማኔጅመት ደረጃ 62 ማናጅሜንት አባላት ውስጥ 20 (32%) የሚሆኑት ሴቶች እንዲሆኑ በማድረግ ድርሻውን ከፍ የማድረግ ሥራ የተሰራ ሲሆን በWomen in leadership፣ ሥርዓተ ጾታ ማካተት፣ የሥራ ፈጠራ፣ ቁጠባና የህይወት ክህሎት ሥልጠናዎችንም እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

127. በሌላ በኩል በዚህ ዓመትም ዓለም አቀፍ የሴቶችና የፀረ-ጾታ ጥቃት፣ የአካል ጉዳተኞች፣ ወጣቶችና የህፃናት ቀን እንዲሁም የኤች አይ. ቪ. ኤድስ ቀናት በተለያዩ ትምህርታዊና የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ተከብሯል፡፡

በተጨማሪም በየ 2 ወሩ በመደበኛነት የሚካሄደው የመ/ቤቱ ሴት ሠራተኞች የልምድ መለዋወጫ መድረክ አሁንም ቀጥሎ በመካሄድ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣በ 119 ሴት ሠራተኞች የእናት ገንዘብ ቁጠባና የብድር አገልግሎት ህጋዊ ሰዉነት እንዲያገኝ እና እንዲቋቋም በማድረግ የካፒታል መጠኑ 529,722.61 የደረሰ ሲሆን ከዚህም ሴት ሠራተኞች አባላት የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፣

128. የስራ አካባቢን ምቹ ከማድረግ አንጻር የሠራተኞች ክበብ በተመጣጣኝ ዋጋ የምግብ አገልግሎት ለሰራተኞች ሁሌም እንደሚደረገዉ በዚህ አመትም አገልግሎቱ እየቀረበ ሲሆን የመሠረታዊ ሸቀጣ ሸቀጦችን እና ሌሎችንም ግብዓቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ለሠራተኛው በማቅረብ የኑሮ ዉድነቱን ጫና ለማገዝ ጥረት ተደርጓል፡፡

129. ሁሌ እንደሚደረገው በዚህ አመትም የመስክ የሥራ ድልድል ሲደረግ ለሴት ኦዲተሮች ቅድሚያ በመስጠትና ምቹ የሆነ የሥራ ቦታ ምደባ እንዲያገኙ በማድረግ በስራ ስምሪት ድልድል ወቅት ቅድሚያ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

<u>የአቅም ግንባታ እና ከኦዲት ባለድርሻ አካላት ጋር የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ፣</u>

130. ለኦዲት ስራም ሆነ ለሌሎች ስራዎች ቀጣይነት ያለው ስልጠና መስጠት መሰረታዊ ጉዳይ በመሆኑ በመስሪያ ቤታችን ራሱን የቻለ የሥልጠና ተቋም ለመገንባት በስትራቴጅክ ዕቅድ ተይዞ ቅድመ ሁኔታዎችን እያመቻቸን እንገኛለን፡፡ ነገር ግን ይህ ተግባራዊ እስኪሆን ድረስ በተቋሙ የተዘጋጁ 5 የሚሆኑ የስልጠና ክፍሎችን በማደራጀት ስልጠና እየሰጠን ብንቆይም ህንጻው በእድሳት ላይ ስለሆነ ባቅራቢያችን ከሚገኙ ተቋማት አዳራሾችን በመጠቀም እና በተለያየ ቦታዎች ስልጠናዎችን እየሰጠን የምንገኝ ሲሆን በእድሳት ላይ ባለው ህንጻ ቀድሞ ከነበረው ተጨማሪ 2 የስልጠና ክፍሎችን እንዲኖሩት በማድረግ በቅርቡ ተጠናቆ ስራ የሚጀምር ይሆናል፡

131. መ/ቤታችን አሁን ያለውን የስልጠና ማዕከል ለማሳደግ Concept note በማዘጋጀት ለአሜሪካ ጂ.ኤ.ኦ (GAO) አስተያየት እንዲሰጡ እና ሌሎች አስፈላጊ ቴክኒካል ድጋፎችን ማድረግ እንዲችሉ የተላከ ሲሆን ይህን አህጉራዊ ተቋም ለመገንባት የክልሎች ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ ሁሉም የክልል ዋና ኦዲተሮችን በማሳተፍ ኢንስቲትዩቱን ለማቋቋም የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ በጋራ መድረክ ውይይት በማድረግ ይህን የሚያስተባብሩ ኮሚቴ አባላት በክልሎች እንዲመረጥ ተደርጎ ሥራው በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

132. በመ/ቤቱ በ2016 ዓ.ም 30 ለድጋፍ ዘርፍ እና 39 ለኦዲት ዘርፍ በድምሩ 69 ዓይነት የሥልጠና ፍላጎቶችን በመለየት በማኔጅመንት በማጸደቅ የሥልጠና ካላንደር እንዲዘጋጅ ተደርጓል፤ በፀደቀው ካላንደር መሰረትም ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

133. በዚህም መሰረት ለ6 ሠራተኞች የውጭ አገር ሥልጠና በተለያዩ ርዕሶች፣ በፋይናንስና ህጋዊነት ዘርፍ ለ352 ሠራተኞች፣ በክዋኔ እና አከባቢ ኦዲት 68 ሠራተኞች፣ በድጋፍ ዘርፍ 69 እና ለባለድርሻ አካላትና ክልል ዋና ኦዲተሮች ደግሞ 791 ሠራተኞች አቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

134. በሌላ በኩል 10 ሠራተኞች የኤሲሲኤ (ACCA) ትምህርት እድል በዚህ አመት ያገኙ ሲሆን በትምህርት ላይ ላሉ 20 PESAI-P ትምህርት ለሚማሩ ተማሪዎች ድጋፍና ክትትል ተደርጓል ።ከዚህ 2 ሰራተኞች ያጠናቀቁ እና 18 በመማር ሂደት ላይ ናቸው፡፡

135. እንዲሁም በቀጣይ ወደ ትምህርት የሚገቡ 26 ሰራተኞች የሁለተኛ ዲግሪ ለመማር የመግቢያ ፈተና እንዲወስዱ የተደረገ ሲሆን በተጨማሪም 10 ሰራተኞች IDI (INTOSAI development initiative) በሚሰጠዉ professional Education for SAI-P (PESAI-P) የአንድ ዓመት ትምህርት በኦን ላይን (online) ለመማር ተመርጠው ለሚያስተምረው ተቋም እንዲላክ ተደርጓል፡፡

እንዲሁም ለሌሎች አካላት አቅም ግንባታ ድጋፍ ከማድረግ አንጻር ለ7 ክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች፣ለ10 ኦዲት ተደራጊ ሚ/ር መ/ቤቶች ፣ በተጨማሪም ለፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ መምሪያ እና አቃቤ ህግ እና ለመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ተሰቷል፡፡

<u>የኦዲት ባለድርሻ አካላት የጋራ መድረክ እና መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግን በተመለከተ፤</u>

136. ቋሚ ኮሚቴው በዚህ በጀት አመት ባዘጋጃዉ 21 ይፋዊ ህዝባዊ ስብሰባዎች እና 9 የመስክ ጉብኝቶ ላይ በመገኘት በተነሱ ጉዳዮች ላይ ተገቢዉን ማብራሪያና ማስረጃ በመስጠት ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም በመ/ቤቱ የተሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች፣ ይፋዊ የዉይይት መድረኮች፣ የተለያዩ መድረኮችና ሁነቶች፣ የሚዲያ ዳሰሳ ውጤቶችን፣ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ጽሁፎች እንዲሁም በተለያዩ በ15 ጋዜጦች ላይ የመ/ቤቱን የተለያዩ ጉዳዮች በሚመለከት የወጡ ዘገባዎችን የመለየት እና የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡፡

137. የዋና ኦዲተሮች ጉባኤ በቦንጋ ከተማ እንዲሁም 22ኛው ከባለድርሻ አካላት ጋራ በሚደረገው የዋና ኦዲተሮች እና የባለድርሻ ጉባዔ በሃዋሳ ከተማ ተካሂዷል፡፡

138. የ4 ዓመታት (ከ2011-2014 ዓ.ም) የተጠቃለለ የኦዲት ሪፖርት ቡክሌቶች ታትመው ለየፌዴራል ተቋማት የማሰራጨት ስራ ተሰርቷል፡፡

<u>የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ሁኔታ</u>

139. ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል የኦዲት ባለሙያ 669፣ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ 344 በድምሩ 1013 ሲሆን፡፡ ስራው ሲጀመር የነበረው የሰው ሃይል 489 ኦዲተሮችና 197 የድጋፍ ሰጪ በድምሩ 686 ሠራተኞች በሥራ ላይ ነበሩ፡፡ በኦዲት ዓመቱ ውስጥ 12 ሰራተኞች ለድጋፍ ዘርፍ እና 29 ለኦዲት ዘርፍ በድምሩ 41 ሠራተኞች ተቀጥረዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከስራ የለቀቁት በገዛ ፈቃዳቸው ከኦዲት 39፣ ከድጋፍ 3 በጡረታ ደግሞ 6 ሰራተኞች ባጠቃላይ 48 ሰራተኞች በተለያየ ምክንያት መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡

140. በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ 482 የኦዲት ባለሙያዎች (323 ወንድ እና 159 ሴት)፣ 197 የድጋፍ ሰጪ (88 ወንዶችና 109 ሴቶች) ሠራተኞች በአጠቃላይ 679 ሠራተኞች በሥራ ላይ ይገኛሉ፡፡ ክፍት የሥራ መደቦችን ለማሟላት በየወቅቱ ከፍተኛ ጥረት የሚደረግ ቢሆንም ባለው የሠራተኛ ፍልሰት እና በተለይ የስራ ባህሪው በአብዛኛው በመስክ አመቺ ባልሆኑ አከባቢዎች ጭምር የሚከናወን በመሆኑ የውሎ አበል ማናስ ምክንያት ሰራተኛው ተቋቁሞ መስራት በመቸገሩ ችግሩን ማስወገድ አልተቻለም፡፡

<u>የ2015 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀም፣</u>

141. ለ2015 በጀት ዓመት በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ መደበኛ በጀት **ብር 160,523,312.38** የተፈቀደ ሲሆን ለዓመቱ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ **ብር 159,133,964.97 (99.13%)** መጠቀም ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሰየማቸው ገለልተኛ ኦዲተሮች ኦዲት በመከናወን ላይ የሚገኝ ሲሆን እንደተጠናቀቀ ለም/ቤቱ የሚላክ ይሆናል፡፡

2016 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር የበጀት አጠቃቀም፣

142. ለ2016 በጀት ዓመት በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ መደበኛ በጀት **ብር 174,406,840.00** እና ለመ/ቤቱ ህንጻ እድሳትና ቁሳቁስ 150,000,000.00 በድምሩ **ብር 324,406,840.00** የተፈቀደ ሲሆን ለዓመቱ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ በዘጠኝ ወራት ጊዜ ውስጥ ለመጠቀም ከመደበኛ በጀት የታቀደ **ብር 131,242,618.00** ሲሆን በዕቅዱ መሠረት **ብር 133,003,028.00 (101.34%)** መጠቀም ሲቻል ለህንጻና ቁሳቁስ እድሳት በ9 ወራት ውስጥ 120,000,000.00 ለመጠቀም የታቀደ ቢሆንም አፈጻጸም **ብር 84,498,267.00** (70.42) መጠቀም ተችሏል፡፡ የተቀረው በጀት **ብር 41,403,812.00** ከመደበኛ እና **ብር 65,501,733** በድምሩ **ብር 106,905,545** በቀሪ ወራት ውስጥ ለማከናወን የታቀደ ሲሆን ዕቅዱን ለማሳካት የፈርኒቸር ግዥ ውል ተገብቶ እየቀረበ የሚገኝ እና የህንጻ ግንባታ የክፍያ ሰርተፊኬት የቀረበ በመሆኑ በጀቱን በአቅዱ መሰረት መጠቀም ተችሏል ፡፡

143. ከሀምሌ 2015 እስከ መጋቢት 30/2016 ድረስ ከፕሮጀክ በጀት **ብር 39,629,676.00** ወደ መ/ቤቱ አካዉንት የተላለፈ ሲሆን አጠቃቀሙም **ብር 33,868,096.00 (85.46%)** ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን በፕሮጀክቱም 3 መኪና እና 25 ላፕቶፖች ግዥ በገ/ሚ/ር በኩል ተከናውኖ ተረክበን ሥራ ላይ እንዲውሉ አድርገናል፡፡

144. ሌላው ከወጪ ቅነሳ ጋር በተያያዘ የቢሮ ዕድሳት በሚደረግበት እዛዉ ቢሮውን ከፋፍሎ እና አሸጋሽጎ በመጠቀም ወጪ ለመቆጠብ ታስቦ ያለ ቢሮ ኪራይ መገንባት ተችሏል፣ በዚህም በአማካይ በወር **ብር 2,300,000.00** በ18 ወር ሊወጣ የነበረውን **ብር 41,400,000.00 ሚሊዬን** ማዳን ተችሏል፡፡
የንብረት አወጋገድን በተመለከተ አሮጌ የማያገለግሉ 130 የሚሆኑ ላፕቶፕ ኮምፒዩተር እና የኮምፒዩተር ሲስተም (CPU) **ብር 639,900.00** ተሽጦ ለገንዘብ ሚኒስቴር ገቢ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

የዉስጥ ቁጥጥር ስርዓትን በተመለከተ

145. መ/ቤቱ የተመደበለትን በጀት በአግባቡ መጠቀሙን እና ለታመለት አላማ ማዋሉን ከማረጋገጥ አንጻር በውስጥ ኦዲት በየሩብ አመቱ ኦዲት እየተደረገ ሲሆን በዉጭ ኦዲትም የ2014 በጀት አመት ፓርላማው በሰየማቸው የውጭ ኦዲተሮች ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ለም/ቤቱ ቀርቧል።

የኦዲት አስተያየቱም ከስህተት የጸዳ ሲሆን የ2015 በጀት አመትም ፓርላማዉ የተሰየማቸው የዉጭ ኦዲተሮች በ27/09/2016 የኦዲቱን ስራ ጀምረዋል፡፡

146. የ2016 በጀት ዓመት የግዥ እቅድ በ e-GP ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት እየተፈጸመ ይገኛል፡

147. የመስክ ተሽከርካሪዎች የቴሌ ብር ወይም የሲ.ቢ.ኢ. ብር አግልግሎት ደረሰኝ ብቻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተደረገ ሲሆን በቀጣይ ተሽከርካሪዎችን በጂፒኤስ ለመቆጣጠር እንዲቻል ጨረታ ወጥቶ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ ተቋማችን በፈጸማቸው ክፍያዎች ላይ ተቀንሰው መቅረት ያለባቸውን የተጨማሪ እሴት ታክስ **ብር 6,016,184.62**፣ ዊዝሆልዲንግ ታክስ **ብር 1,632,766.33** የወጪ መጋራት (cost sharing) **ብር 72,190.17** በድምሩ **ብር 7,721,141.12** ተሰብስቦ ለገቢ ሰብሳቢዉ መ/ቤት ገቢ ተደርጓል፡፡

148. የተቋሙ የ2015 የንብረት እና የጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ ቆጠራ መሠረት የፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ የ2015 4ኛ ሩብ ዓመት የመደበኛ እና የአይፒኤፍ ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት የቀረበ ሲሆን፣ የ2016 በጀት ዓመት የ1ኛ እና 2ኛ ሩብ ዓመት ሂሳብ ኦዲት በውስጥ ኦዲት ተከናውኗል፡፡ የ2015 በጀት ዓመት የሰራተኞች መዝናኛ ክበብ ሂሳብ ኦዲት ተደርጓል፡፡

<u>የህንጻ ግንባታ አፈጻጸምን በተመለከተ፡</u>

149. ከፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ጋር በተደረገ ህጋዊ የስራ ውል መሰረት ጂ+10 የህንጻ እድሳት ስራ እየተከናወነ ሲሆን፣ ከፊሉ የህንጻው ክፍል እድሳት ተጠናቆ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፤ ቀሪዉ የህንጻ ክፍል እድሳቱ ተጠናቆ ህምሌ 1/2016 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ ስራው ይጀምራል ተብሎ ይጠበቃል። ቀሪ ሥራና የቢሮ መገልገያ ቁሳቁስ በአዲስ የሚሟላት ስራዎች በመጪዎቹ ጥቂት ወራት ውስጥ የሚጠናቀቁ ይሆናል፡፡

<u>ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በተመለከተ፣</u>

150. የመ/ቤቱ ሥራዎች በቴክኖሎጂ በማስደገፍ የኦዲት አሠራር የሚያዘምኑና የመ/ቤቱን የመረጃ ስርዓቶች ተመጋጋቢ እንዲሆኑ የሚያደርጉ የመ/ቤቱን ሥራ ከማቀላጠፍ፣ ወረቀት አልባ ተቋም ከማድረግ አንጻር ባለፉት አመታት ስራዎች ሲሰሩ የቆዩ ሲሆን የኦዲቱን ስራ በሲስተም በማገዝ ምቹ እና ቀላል ለማድረግ ስራዎቻችንን በቴክኖሎጂ የማዘመን ስራ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

151. የመስሪያ ቤቱን ስራ በቴክኖሎጂ ከመደገፍ አንጻር ወይም (Application Portal) ሥርዓቶች በመዘርጋት፡- የሰው ሃብት (HRMS)፣ ግንኙነት ስርዓቶች IP Telephony፣ IPTV System፣ የቁጥጥር ስርዓቶች IP Surveillance System፣ Time Attendance System፣ ኮርፖሬት ኢሜል (Corporate E-Mail)፣ ድረ-ገፅ (Website)፣ የኢንተርኔትና ወረዳኔት አገልግሎት ክትትል፣ አገልግሎት አሰጣጥ አስተዳደር ስርዓት (Helpdesk Management System) , eGP እና የተቀናጀ ፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት (IFMIS) ትግበራን በእድሳቱ ምክንያት መቆራረጥ ቢኖርም በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ተደርጓል፡

<u>የተከናወነ የክትትል ሥራን በተመለከተ፡</u>

152. ከዚህ በፊትም ሲደረግ እንደነበረዉ ሁሉ የክትትል እና የቁጥጥር ስራ በዳይሬክተር እና በሥራአስኪያጆች አማካይነት በመስክ ክትትልና ድጋፍ የተደረገ ሲሆን እያንዳንዱ ቡድን የተሰሩ ስራዎች ላይ በየሣምንቱ፣ ሥራ አስኪያጆች ከከፍተኛ ኦዲተሮች ጋር በየ15 ቀኑ፣ ዳይሬክተሮችና ሥራ አስኪያጆችም በየ15 ቀኑ እንዲሁም ማናጅሜንቱ በየወሩ በመገናኘት አፈጻጸሙን በመገምገም አስፈላጊውን ግብረ መልስ የመስጠት ሥራዎች ተከናውኗል፡፡

<u>መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮና የተወሰዱ እርምጃዎች</u>

153. በአፈጻጸም ወቅት መ/ቤቱን ካጋጠሙት ችግሮች መካከል አብዛኛዎች ባለፈዉ አመትም የነበሩ አሁንም የቀጠሉ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ፡- የቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር የመረጃ ሥርዓት (IFMIS) ፣ eGP እና የገቢዎችና ጉምሩክ የሲስተም መቆራረጥ እንዲሁም በፀጥታ ምክንያት ሥራዎችን በታቀደው ዕቅድ መሠረት ማጠናቀቅ አለመቻል፣

154. በቢሮ ዕድሳት ምክንያት ማስረጃ ማቅረብ ባለመቻሉ ኦዲት ያልተደረገ መ/ቤት መኖሩ፣

155. የመ/ቤት ኃላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት አለመገኘትና የኦዲት ጊዜውን ማጓተት እንዲሁም ከመውጫ ስብሰባ በኋላ በርካታ ዶክመንቶች አሉን በማለት ለማጣራት ተጨማሪ ጊዜ በመውሰዱ ኦዲቱ በወቅቱ እንዳይጠናቀቅ ማድረጉ፣

156. ለኦዲት ተደራጊዎች ለሚላኩ የኦዲት የስራ ወረቀቶች እና ረቂቅ ሪፖርቶች በወቅቱ ምላሽ አለመስጠት፣

157. የሂሳብ ሪፖርቶችን በወቅቱ ዘግቶ አለማቅረብ፣ የሥራ ቢሮና የሂሳብ ዶክሜንቶች በተቀመጠ ጊዜ ገደብ ዉስጥ ተዘጋጅቶ ለኦዲት ሥራ አለማድረስ፣ ለሥራ የሚያስፈልጉ በወቅቱ ማቅረብ አለመቻል፣

158. ካለው የኑሮ ውድነት ጋር ተያይዞ ለመ/ቤቱ ሠራተኞች ከመ/ቤቱ ተጠንቶ የቀረበው የውሎ አበል በኦዲት ኮሚሽኑ አስተያየት ተሰጥቶበት ለም/ቤቱ ቀርቦ እንዲም በም/ቤቱ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ይሁንታ አግኝቶ በዚሁ መሰረትም በፓርላማ ጽ/ቤት በኩል ለገ/ሚር ቢላክም እስካሁን ምላሽ የተሰጠበት ሁኔታ ባለመኖሩ በመ/ቤቱ ሠራተኞች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከመድረሱም በላይ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው የባለሙያ ፍልሰት እያስከተለ የሚገኝ ስለሆነ የተከበረው ምክር ቤት ትኩረት እንዲሰጥበት በአክብሮት እጠይቃለሁ።

159. ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ጋር በመነጋገር ለመፍታት ጥረት ተደርግዋል። በተጨማሪም ያልተፈቱ ችግሮች ቢኖሩም ችግሩን በመቋቋም ስራዎቻችንን በአቀድነው መሰረት ጥሩ በሚባል አፈፃፀም ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ የሰራተኛ የውሎ አበል በተመለከተ ሰራተኛው ሥጋት ያለበት አከባቢዎች በመስራት በ300 ብር ቁርስ፣ ምሳ፣ እራት እና አልጋ ሸፍነህ ሥራ መባሉ በሠራተኛው ላይ አሉታዊ ስሜት የፈጠረ በመሆኑ የዚህን መስሪያ ቤ/ት ጥያቄ መመለስ ትንሽ ሰጥቶ ብዙ የሚተረፍበት በመሆኑ የተከበረዉ ም/ቤት ጉዳዩን በአንክሮ አይቶ ምላሽ እንዲሰጠበት በአክብሮት እጠይቃለሁ።

160. በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ሀላፊነታቸውን የተወጡትን ሰራተኞች በም/ቤቱ ፊት ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡

የመንግስት ልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ኦዲት ክትትል፣

161. በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲታቸው የተከናወኑ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 47 እና በኢትዮጵያ መንግሥትና በልማት አጋር ድርጅቶች የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ኦዲት 105 በድምሩ 152 ሪፖርቶች እስከ የካቲት 30/2016 በማጠናቀቅ ሪፖርቶቹ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲላክ ተደርጓል፡፡

162. በዚሁ መሰረትም የመንግስት የልማት ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት ሲተነተን አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 26፣ ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆንም ነቀፌታ ያለበት (Qualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 13፣ አቋም ለመውሰድ የማይቻል በመሆኑ አስተያየት ያልተሰጠባቸው (Disclaimer Opinion) 5 እና ተቀባይነት የሚያሳጣ የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው (Adverse opinion)3 ሲሆን የፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ኦዲቶች በኦዲት አስተያየት ሲተነትን አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 80፣ ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆንም ነቀፌታ ያለበት (Qualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 19፣ አቋም ለመውሰድ የማይቻል በመሆኑ አስተያየት ያልተሰጠባቸው (Disclaimer Opinion) 3 እና ተቀባይይነት የሚያሳጣ የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው (Adverse opinion) 3 ናቸው፡፡

<u>የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ ዕቅድና ክንውን፣</u>

163. ኮርፖሬሽኑ የገቢ ምንጭ በዋናነት የተመሰረተው ለተለያዩ የመንግስት የልማት ድርጅቶችና ሌሎች መንግስታዊ ተቋማት (ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች) ከሚሰጠው የኦዲት አገልግሎት ክፍያ፣ ከማማከር እንዲሁም ከሕንፃው ቢሮዎች ከሚገኝ የኪራይ ገቢ ሲሆን ኮርፖሬሽኑ በ2015 በጀት ዓመት ብር **75,693,443** ገቢ ለማግኘት አቅዶ ብር **98,043,555** ገቢ ያገኘ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ብር **71,687,589 ወጪ** ለማድረግ አቅዶ **ብር 62,462,331** ወጪ ያደረገ ሲሆን ብር 2,804,098 የተጣራ ትርፍ ለማግኘት አቅዶ **ብር 24,906,857** ሊያገኝ ችሏል፡፡

<u>የ2016/17 ኦዲት ዓመት ዕቅድ፣</u>

164. የ10 አመቱን መሪ እቀድ መነሻ ተደርጎ የተዘጋጀውን የመ/ቤቱ የ5 ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ በቴክኒክ ኮሚቴ፣ በስቲሪንግ ኮሚቴ፣በማናጅመንት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ተገምግሞና አስታያየት ተሰጥቶበት ወደ ትግበራ የተገባ ሲሆን እንደገና በ2015 በጀት አመት የእስትራቴጂክ ዕቅድ አጋማሽ አመታት ግምገማ በማድረግ ተከልሶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡

በዚህም መሠረት በ2016 በጀት ዓመት በጀት ከተመደበላቸው 183 የፌዴራል መ/ቤቶች እንዲሁም 54 ቅርንጫፎች ውስጥ ቀደም እንዳሉት ዓመታት 14 የሚሆኑት ሂሳባቸው በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት እንደሚደረጉ ታሳቢ ተደርጎ የተቀሩትን 169 መ/ቤቶች 54 ቅርንጫፎች በመ/ቤታችን ኦዲት በማድረግ የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ሽፋኑን 100% ለማድረስ ታቅዷል፡፡ እንደዚሁም ከመጋቢት 2016 እስከ ጥር 2017 ድረስ ባለው ጊዜ 24 አዳዲስ የክዋኔ፣ 8 የአከባቢ ኦዲቶችን እና 8 ክትትል፣ 2 የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሲስተም ኦዲቶችን በማከናወን 42 የክዋኔ፣ አከባቢ እና የኢንፎርሜሽን ሲስተም ኦዲት ሪፖርቶችን ለማውጣት ታቅዷል፡፡ በተጨማሪም በድጋፍና ድጎማ 368 የኢንቨስትመንት ፋይናንስ ፕሮጀክት ኦዲት፣13 ማረጋገጫ ኦዲት (Verifications)፣ 1 የተጠቃለለ የክልሎች ኦዲት፣ የገንዘብ ሚ/ር የተጠቃለለ ሂሳብ ኦዲት እንዲሁም 13 የመሰረታዊ አገልግሎት ለሁሉ አቀፍ ፍትሐዊ ዕድገትና ተጠቃሚነት (Enhancing Shared Prosperity through equitable service) ኦዲቶችን በአጠቃላይ 395 ኦዲቶችን እና የፌደራሉ መንግስት ለክልሎች የሚሰጠውን በጀት እና ድጎማ በ12 ክልሎች እና በ2 የከተማ አስተዳደር ለማከናወን በዕቅድ ተይዟል፡፡

ማጠቃለያ

165. የ2015 በጀት አመት ሂሳብ ላይ የተካሄደው የፋይናንስ እና ህጋዊነት ኦዲት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የታቀዱትን ጨምሮ በወቅታዊ ሁኔታ ከተቋረጡት 11 መ/ቤች እና 4 ቅርንጫፎች በስተቀር በተቀሩት የፌደራል ባለበጀት መ/ቤቶች ኦዲቱ ተከናዉኗል፡፡ አፈጻጸሙም 94..44% ሆኗል።

166. በሌላ በኩልም የክዋኔ ኦዲትን እቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ 32 አዲስ፣ 12 የክትትል ኦዲት በድምሩ 44 ለመስራት ታቅዶ የ32 ኣዳዲስ ኦዲት እና 11 የክትትል ኦዲት በድምሩ የ43 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ወጪ ተደርጓል። አፈጻጸሙ 97.72% ሆኗል፤ አንድ የክትትል ኦዲት በሰው ኃይል ምክንያት ስራውን መስራት አልተቻለም።

167. የልዩ ኦዲት እቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ በእቅድ የተያዘው 11 ሲሆን በበጀት አመቱ 26 ጥያቄዎች የቀረቡ በመሆኑ ሌሎች የኦዲት የስራ ክፍሎች በተጨማሪ እንዲሰሩ በማድረግ አፈጻጸሙ 23 ሆኗል። የተሰራው ልዩ ኦዲትም ለጠየቀው አካል እንዲደርስ ተደርጓል።

168. የኢትዮጵያ መንግስት እና የአለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሰረት የፍትሃዊነት መሰረታዊ አገልግሎት ለሁሉ አቀፍ የእድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራምን የተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ከሆኑ ክልል ወረዳዎች 337 ለመስራት ታቅዶ 345 መስራት ተችሏል። አፈጻጸሙም 102.37% ሆኗል፡፡

169. የ2015 በጀት አመት የኦዲት ውጤት ሲታይ ነቀፌታ የሌበት 79፣ ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር አጥጋቢ ሆነው የተገኙ 50 አሰተያየት መስጠት ያልተቻለባቸው 7 የጎላ ችግር ያለባቸዉ ሆኖ በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸዉ 15 አጠቃላይ ዉጤቱ ሲታይ ነቀፌታ የሌለበት ከጥቂት ጉድሎቶች በስተቀር ባጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው የተገኙ እና ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው የተወሰነ መሻሻል ያልታየበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

170. የግኝቶቹም ባህሪ ሲታይ የመጨመር እና የመቀነስ ጉዳይ ካልሆነ በቀር እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ የ2015 በጀት አመትም ዋነኛ ሆነው የቀጠሉት መጠኑ ቢቀንስም የጥሬ ገንዘብ ጉድለት አሁንም የቀጠለ መሆኑ፣ የውዝፍ እና ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ አለመሰብሰብ እና አለማወራረድ፣ በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ አዋጅ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ገቢን አለመሰብሰብ፣ ደንብ እና መመሪያዎች ያልጠሰብቁ ግዢዎችን የዉስጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀም የበጀት አስተዳደር እና አጠቃቀም በብልጫ የተከፈለ ክፍያዎች የመንግስት ንብረት አጠቃቀም እና አስተዳደር የሚታዩ ጉድለቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በሌላ በኩልም በበጀት አመቱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በተደረገ ክዋኔ ኦዲቶች በርካታ ሊዘረጉ የሚገባ የአሰራር ስርዓቶች አለመዘርጋት እና አለመተግበር ፣ በመ/ቤት ዉስጥም ሆነ ከሌሎች ተቋማት ጋር የቅንጅት እና የትብብር ጉድለቶች መኖር፣ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው በጀት እና ግዜ አለመጠናቀቅ፣ በእቅድ የተያዙ ስራዎችን በእቅድ መሰረት አለመፈጸም ዋና ዋና ግድፈቶች ሆኖ ተገኝቷል፡፡

171. አጠቃላይ በኦዲቱ የተገኙትን የአሰራር ጉድለቶች እና ክፍተቶች ለማረም እና ለማስተካከል የሚያስችሉ የመፍትሄ ሃሳቦችን ጭምር ያካተቱ ከመሆኑም በላይ አብዛኛዎቹ የተሰጡት ማሻሻያ ሃሳቦች በኦዲት ተደራጊዎች ጭምር ስምምነት የተደረሰባቸው ናቸው።

172. ስለዚህ ዝርዝር የፋይናንስ እና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቱ አጠቃላይ ዘገባ ልዩ ልዩ ዘገባ በሁለት ጥራዝ እንዲሁም እያንዳንዱ የክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ሪፖቶች እና ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሳጣቸው መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርቶች ተደራጅተዉ በሶፍት ኮፒ ለተከበሩ አፈጉባኤ የተላኩ በመሆኑ ሪፖርቶቹን የም/ቤቱ የመንግሰት ወጪ አስተዳደር ቁጥጥር ጉደዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች ጭምር በጥልቀት ታይተው እና ተመርምረው ተገቢዉ እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል እና ቁጥጠር ቢደረግ።

173. የተጠያቂነትን ስርዓት ከማረጋገጥ አንጻር የመንግስት ወጪ አስተዳደር ቁጥጥር እና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ግልጽ የሆነ ይፋዊ የህዝብ ዉይይት በማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ተጠያቂነት እንዲሰፍን የተሰራው ስራ የሚያበረታታ ነው፡፡ በተጨማሪም ገንዘብ ሚ/ር በተሰጠው ስልጣን እና ተግባር መሰረት በተጨማሪም ከቋሚ ኮሚቴው በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የኦዲት ሪፖርትን መነሻ አድርጎ የወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ እና የም/ቤቱ የተለያየ ቋሚ ኮሚቴዎች ኦዲቱን መሰረት በማድረግ ክትትል ማድረጋቸው የመ/ቤት አመራሮች ለኦዲቱ ትኩረት እንዲሰጡ አስተዋጽኦ አድርጓል። ይህ አካሄድ የበለጠ ተጠናክሮ እንዲቀጥል በአክብሮት እየጠየኩ በይፋዊ ህዝባዊ ውይይት ወቅት አብረውን ለነበሩ ባለድርሻ አካለትም ላደረጉት አስተዋጽኦ እንዲሁም ሁሉንም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በኦዲቱ ወቅት ላሳዩት ትብብር በኔ እና በመ/ቤቱ ስም እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ። በጥሞና ስላዳመጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ።

አባሪ 1

<u>የልዩ ኦዲት ስራዎች</u>

1. ድል በትግል የገበያ አ.ማ
2. የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
3. የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን
4. የኢትዮጵያ ልማት ባንክ አዳማ ቅርንጫፍ
5. የኢትዮጵያ ፓራ ኦሎምፒክ ኮሚቴ
6. የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ የ2011 በጀት ዓመት የተለያዩ ግዢዎች
7. የኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ
8. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት
9. ግዮን ሆቴል ድርጅት
10. አንድ ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ
11. የትምህርት ሚኒስቴር
12. የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ
13. የአዲስ ትውልድ ፓርቲ
14. የመቱ ዩኒቨርሲቲ
15. የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ
16. እንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት
17. ህብረት ሥራ ኮሚሽን
18. የጣና ሐይቅ ትራንስፖርት ድርጅት
19. ፈለገ ህይወት ሆስፒታል
20. የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር
21. ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ
22. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት

23.ቢኤም ኢትዮጵያ ስፌት እና ጨርቃ ጨርቅ አክስዮን ማህበር ናቸው፡፡

አባሪ 2

	ሂሳባቸውን በወቅቱ ያልዘጉ መ/ቤቶች
	የመ/ቤቱ ስም
ተ.ቁ	**ፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች**
1	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
2	የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት
3	የኢትዮጲያ ኮሚዩኒኬሽን ባለሥልጣን
4	የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት
5	የፕላንና ልማት ሚኒስቴር
6	ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
7	የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
8	የኢትዩጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ
9	ኢሚግሬሽነና ዜግነት አገልግሎት
10	ትራንስፖርትና ሎጀስቲክ ሚኒስቴር
11	የፌዴራል ፖሊስ ኮምሽን
12	የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት
	የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች
1	አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ
2	የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር
3	የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ
4	የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት
5	ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ
6	የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር
7	ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ
	የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች
1	የኢትጵያ ደን ልማት